

የጥንቱ የዋልድባ ገዳም ቤተ ክርስቲያን

ዋጋው አንድ ብር

# ትንሣኤ




ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌላዊ

ቁጥር ፲፬

መስከረም ፲፱፻፸፯ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ እምነትና ታሪክ፣ ሥርዓትና ዜና፣ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጉሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»


አዘጋጅ
ልማትና ወርቅ ሰባሰበ ፤
ም በሰ.ጠ ሰጠ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

## ማውጫ

| ርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| አርጌውን ሰውነት ከክፉ ሥራው ጋር ተውት | ፪ |
| የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቃለ ቡራኬ | ፬ |
| አክሊለ በረከት | ፭ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን | ፯ |
| አብር የበላን ቅዱስ ዮሐንስ አይሽረውም | ፱ |
| ሥዕለ ማርያም በዓዴንያ | ፲፩ |
| መስቀል ኃይላችን ነው | ፲፫ |
| በፀበሉ ፈዋሽነት የታወቀው ማቢ አቦ መካነ ሕይወት ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ ተጸበረ | ፲፭ |
| የዋልድባ ገዳም ታሪክ | ፲፯ |
| ዜና ሊታወቁንት | ፳ |
| አንጢላርዮስ | ፳፩ |
| ጠባቆችን እሰጣችኋለሁ | ፳፪ |
| ቅድስት አርሴማ | ፳፬ |




ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ የእግዚአብሔር አባታችን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን እያልኩ መንፈሳዊ ሰላምታየን ሳቀርብ በትሕትና ነው ።

ከሰላምታዬ ቀጥዬ በአእምሮዬ ሲጉላሉ የኖሩ ጥያቄዎችን አቀርባለሁ ።

፩/ ክህነት የሌለው ሰው መስቀል ይዞ ማጥመቅ ይፈቀድለታልን ፤ በደብረ ዘይት ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ክህነት የሌለው ትምህርትም ያልተማረ በዘፈቀደ ባሕታዊ ነኝ የሚል ሰው ሕሙማንን ሲያጠምቅ በማየቴ ይህንን ጥያቄ አቅርቤያለሁ ።

፪/ በሰባካ ጉባኤ ተመዝግቦ አስተዋጽኦውን የከፈለ ሰው ከቤተ ሰቡ ሰው ሙቶበት ወይም ራሱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ፍትሐት ፍቱ ተብለው አንዳንድ ካህናት ሲጠየቁ ፵ ብር ያስከፍላሉ በተጨማሪም ሦስት እንስራ ጠላ ፵ እንጀራ እንዲከፈል ያስገድዳሉ ይህ አሠራር ተገቢ ነውን ?

፫/ እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የራሷ የሆነ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አላት ሥርዓቱ ግን አልፎ አልፎ ሲሻር ይታያል ለመሆኑ ማንኛውም የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ የሆነ ሰው በጾም ወራት በተክሊል መጋባት ይፈቅድለታልን ? ካልተፈቀደስ ይህንን የፈጸመ ክርስቲያን ምን ዓይነት ቅጣት ያስፈልገዋል ?

፬/ አንድ ዲያቆን ያለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ከሜዳ ጠልፎ ወስዶ አግብቶ ቅስና መቀበል ይችላልን ?

፭/ ስብከተ ወንጌል በየአብያተ ክርስቲያኑ እንዲሰጥ ቤተ ክህነት ለምን ምሁራንን አይመድብም ?

ከደብረ ዘይት ቅዱስ ሩፋኤል ምእመናን አቶ ቁምላቸው ወልደ መድኅን
ሸዋ

መልስ

አቶ ቁምላቸው ወልደ መድኅን ስላቀረቡልን መንፈሳዊ ሰላምታ እናመሰግናለን ከሰላምታችንም ቀጥለን ላቀረቧቸው ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን ፦

የመጀመሪያው ጥያቄ ሥልጣነ ክህነት የሌለው ሰው መስቀል ይዞ ሕሙማንን በጸበል ማጥመቅ ይገባዋል ? የሚል ነው ጠያቂው ያቀረቡት ጥያቄው ግልጽ አይመስልም የሚያጠምቀው ሰው መስቀሉን ይዞ የሚጠመቁትን በሽተኞች ይባርካቸው እንደሆን ይህ ዓቢይ ስሕተት ስለሆነ ቤተ ክርስቲያናችን በትዕግሥት ልትመለከተው አይገባም። ሕገ ቤተ ክርስቲያንን እንዳፈረሰ ተቆጥሮ የቤተ ክርስቲያናችን ሕግ በሚያዝዘው መሠረት መቀጣት ይገባዋል ፤ ነገር ግን ሳይባርክ ፤ ሳያሳልም በእጁ ወይም በአንገቱ ይዞ ቢያጠምቅ መስቀሉን ለምን ያዘ ተብሎ ሊነቀፍ አይገባውም መስቀል ለተለዩ ሰዎች ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ ክርስቲያን ለተባሉ ምእመናን ሁሉ ነውና ።

ሁለተኛው ጥያቄ በሰበካ ጉባኤ ተመዝግቦ አስተዋጽኦ የሚከፍል ምእመን ከቤተ ሰቡ ሰው ሲሞትበት ወይም ራሱ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ፍትሐት እንዲፈቱ ሲጠየቁ አንዳንድ ካህናት 40 ብር ከማስከፈላቸውም በላይ በ፵ው በ፵ው ሶስት እንስራ ጠላ ፵ እንጀራ ክፈሉ ብለው ያስገድዳሉ ይህ አሠራር ተገቢ ነውን የሚል ነው የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ የሆነው ቃለ አዋዲ በሳበካ ጉባኤ ተመዝግቦ አስተዋጽኦውን ያለማቋረጥ የሚከፍል ምእመን ከቤተሰቡ ሰው ቢሞትበት ራሱም ቢሞት ለጸሎተ ፍትሐት ገንዘብ አይጠየቅም በነፃ ይፈታል ይላል ይህንን ሕግ ማስከበር ያለባቸው የሰበካ ጉባኤው ተመራጮች ናቸው በቃለ ዓዋዲው ደንብ የማይመሩ ካህናት ካሉ ወደ ሚመለከተው ክፍል ማቅረብ ይቻላል።

በሰበካ ጉባኤ ተመዝግበው ሲከፍሉ የኖሩትን ምእመናን በሞት ጊዜ ገንዘብ ካልከፈላችሁ እህል ውሀ ካላመጣችሁ አንፈታም የሚሉ ካህናት ካሉ ይህንን አጉል አስተሳሰባቸውን ትተው የቃለ ዓዋዲውን ሕግ ተከትለው እንዲሠሩ በዚህ አጋጣሚ መንፈሳዊ መልእክታችን እናስተላልፋለን ።

የሦስተኛው ጥያቄ ደግሞ ማንኛውም ክርስቲያን በጾም ወራት በተክሊል መጋባት ይገባዋል ወይ ? የሚል ነው ።

በጾም ወራት እንኳን በተክሊል ያለ ተክሊልም ቢሆን መጋባት እንደማይገባ በፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ ተወስኖአል የቤተ ክርስቲያንን ሕግ አፍርሰው ያገቡ ምዕመናን ቢኖሩ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን በሚያዝዘው መሠረት ንስሐቸውን ይቀበላሉ ።

አራተኛው ጥያቄ አንድ ዲያቆን ያለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ከሜዳ አንዲት ልጅ ጠልፎ ወስዶ አግብቶ በኋላ የቅስና ሥልጣንን መቀበል ይችላልን የሚል ነው ተጠላፊቱ ድንግል ከሆነች ጠልፎ በመውሰዱ ተገቢውን ንስሐ ከተቀበለ በኋላ የቅስናን ሥልጣን ተቀብሎ ከመቀደስ የሚከለክለው ምክንያት የለም ።

ጠያቂው በመጨረሻው ጥያቄዎ ስብከተ ወንጌል በየአብያተ ክርስቲያኑ እንዲሰጥ ቤተ ክህነት ምሁራንን ለምን አይመድብም የሚል ነው ፤ ጥያቄው በጣም የሚደገፍ ነው በቤተ ክህነት ከሚሠሩት ሥራዎች ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባም ስብከተ ወንጌል ነው ። ይህም ስለታመነበት ከቃለ ዓዋዲው መመሪያ ደንቦች ላይ ለስብከተ ወንጌል ከፍተኛ ቦታ ተሰጥቶታል እያንዳንዱ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ለቅዳሴ ሲመድብና ደመወዝም ለእነርሱ ሲደለድል ለሰባኪ ወንጌሉም ደመወዝ መመደብ አለበት ሰባኪ ወንጌል እንዲመደብ መጠየቅ ያለበት ቤተ ክህነት ሳይሆን ሰበካ ጉባኤነውና ጠያቂውም በሚኖሩበት ደብር ሳባኬ ወንጌል ከሌለ ገሰበካውን መንፈሳዊ ጉባኤ ሰባኬ ወንጌል እንዲመድብ የመጠየቅ መብት አለዎትና ይጠይቁ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# “አሮጌውን ሰውነት ከክፉ ሥራው ጋር ተዉት”

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ እግዚአብሔር በምድር ላይ እንዲኖሩ የፈጠራቸውም ፍጥረታት የተለያየ ኅብረ መልክ ያሳያሉ ። አሁን ወርኃ ክረምቱ ተገባዶ የወርኃ መፀው ፈገግን በመታየት ላይ ነው ።

ከአፍ እስከ ደገፋቸው ሞልተው ሰውን እናሻግርም ብለው ከልክለው የነበሩት ወንዞች በመጉደል ላይ ናቸው በጠፈረ ሰማይ እያንገዋበቡ ዝናማትን በየጊዜው ሲያወርዱ የነበሩት ደመናት አንዳንድ ጊዜ ገለጥ እያሉ የሰማይን ኅብረ መልክ ማሳየት ጀምረዋል ። መብረቅና ነጎድጓድም የጉርምርምታ ቃላቸውን በመቀነስ ላይ ይገኛሉ ።

ማር ነጭተው ቅጠል በጥሰው ጥሩ ውሃ ተጉንጭተው የሚኖሩ የቤትና የዱር እንስሳትም የሚፈልጉትን ምግብና ውሃ እንደልባቸው በገፍ በማግኘታቸው ከስተው የነበሩት ወፍረዋል ፤ በረኃብ ምክንያት ኃይል ተነሥ ታቸው ደክመው የነበሩት ኃይል አግኝተው በርትተዋል ።

ነቢዩ ዳዊት ወርኃ ክረምትን አስመልክቶ ሲናገር “ምድርን ጎበኘሃት አጠጣሃትም ፣ ብልጽግናዋ ንም እጅግ አበዛህ የእግዚአብሔር ወንዝ ውሃን የተሞላ ነው ምግባቸውን አዘጋጀህ እንዲሁ ታሰናዳለህና የምድ ርን ትልሟን ታረካለህ ፀሐዩዋንም ታስተካክላለህ በነጠብጣብ ታለሰልሳታለህ ቡቃያዋንም ትባርካለህ በቸርነ ትህ ዓመትን ታቀዳጃለህ ምድረበዳውም ስብን ይጠግባል። የምድረ በዳ ተራሮች ይረካሉ ፡ ኮረብቶችም በደስታ ይታጠቃሉ ማሠማሪያዎች መንጎችን ለበሱ ሸለቆችም በእህል ተሸፈኑ በደስታ ይጮሃሉ ይዘምራሉም ብሏል መዝ. ፷፬.፱-፲፫ ።

ወደ ሰው ልጆች የኑሮ ይዞታ መለስ ብለን ስንመለከት ደግሞ ከሌሎች ሥነ ፍጥረታት የተለየ መልክ እናያለን የሰው ተፈጥሮው ከፍጡራን በላይ እንደመሆኑ መጠን የሚጐዳውንና የሚጠቅመውን እውነቱንና ሐሠቱን ጽድቁንና ኃጢአቱን ለይቶ የሚያውቅበት አእምሮ ከፈጣሪው ተሰጥቶታል ። በዚህ በተሰጠው አእ ምሮ በዚህ ዓለም ሲኖር በአንድ ዓይነት የሥራ መስክ አይሠማራም ፡ ለእያንዳንዱ ሰው የተለየ ስጦታ ስላለው በዚያው በተሰጠው ጸጋ ተሰልፎ በመሥራት ምድራዊ ኑሮውን ያሳልፈዋል ።

ለምሳሌ ገበሬው ያርሳል ነጋዴው ይነግዳል ፡ ምሁሩ ያስተምራል ፤ ዳኛው ይፈርዳል ፡ ሌላውም በሚ ያውቀውና በሚችለው የሥራ መስክ ተሰልፎ ይሠራል ፤ ነገር ግን ዘመን አልፎ ዘመን በሚተካበት ጊዜ ዓመቱን በሙሉ የሠራውን ሥራ ሁሉ የማስተዋልና የመመልከት ግዴታ አለበት ። ነጋዴው ባለፈው ዓመታ የተጠቀ መበትን የንግድ ይዞታ ጠቃሚ መሆኑንና አለመሆኑን ይመረምራል ። ገበሬውም ካለፈው ዓመት አብልጦ ሠርቶ እንደሆነ ወይም ደግሞ አሳንሶ እንደሆነ ሥራውን የመገምገም ፣ ስብሉን የመመልከት ግዴታ አለበት ዳኛውም በበኩሉ የሰጣቸው ፍርዶች ትክክለኛ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን በዓይነ ልቡና ተመልክቶ ስሕተት ቢኖር ለማረም የሚዘጋጀው አሮጌው ዘመን አልፎ አዲሱ ዘመን ሲተካ ሊሆን ይችላል ።

ከላይ ዝናቡን ከታች ጭቃውን ብርዱንና ነፋሱን ፈርተው በስንፍና ሰንሰለት እጅና እግራቸውን ተተብ ትበው ታሥረው ሳይሠሩ በመከረማቸው በችግር አለንጋ የሚገረፉ ሰነፎች ሰዎች የችግር መፍለቂያ የሆነውን ስንፍናቸውን አስወግደው በንቃትና በትጋት ለመሥራት አዲስ መንገድ የሚቀይሱት በአዲሱ ዘመን መጀመሪ ያ ነው ።

ባለፈው ዓመት ጉቦ ተቀብለው መማለጃ በልተው በአምቻ በጋብቻ በወዳጅ በዘመድ ተታለው ትክክለ ኛውን ፍርድ በማዛባት የፈረዱ ዳኞች ቢኖሩ በማይገባ መንገድ የፈጸሙትን ስሕተት ላለመድገም ተጸጽተው በትክክል ለመፍረድ የሚዘጋጁት በአዲስ ዓመት አዲስ ሥራ በሚጀምሩበት ወቅት ነው ።

እንዲሁም በሀሰት የመሰከሩ መሳከርትም ቢኖሩ በአዲሱ ዘመን ስሕተታቸውን ላለመድገም ብዕዓት ይገባሉ ፡ ነጋዴዎችም ባለፈው ዓመት ከሚገባቸው በላይ ያለአገባብ ትርፍን በመሻት ሰውን በድለው እንደሆነ ፡ አቋማቸውን በሚገባ አስተካክለው የሚገባውን አገልግሎት ለተጠቃሚው ሕዝብ በአዲሱ ዘመን ለማቅረብ ይዘጋጃሉ ። መምህራንም የሚያስተምሩትን ትምህርት አሻሽለው ለተማሪዎች ለማቅረብ አስፈላጊውን ዝግጅት ሲያደርጉ ተማሮችም ባለፈው ዓመት በስንፍና ምክንያት ደከም ያሉበትን ማርክ ከፍ ለማድረግ በርትተው



ለማጥናት ታጥቀው የሚነሡት በአዲሱ ዘመን መጀመሪያ ነው ።

ለማስረጃ ያህል ጥቂቶችን ጠቀስን እንጂ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ አሠራሩን አድሶ ለመሥራት የማያ ቅድ ማንም ሰው ይገኛል ብለን አንገምትም ። በአዲስ ዘመን ሁሉም አዲስ ሥራን ቀያሽ ነውና ።

አሮጌው ዘመን አልፎ አዲስ ዘመን ሲተካ የሥራን ይዞታ እያሻሻሉና እያደሱ መሥራት ለማንኛውም ሰው ያስመሰግናል እንጂ አያስነውርም ።

ሐዋርያው ጳውሎስ “አዲሱን ሊጥ ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ” ብሏል ፩ኛ ቆሮ. ፭-፯ አሮ ጌውን ዘመን ሸኝተን አዲሱን ዘመን በምንቀበልበት ጊዜ በአዲሱ ዘመን የምንወጥነው አዲስ ሥራ ሁሉ ፍጻሜ እንዲያገኝ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መዘንጋት አይገባንም ። በኃጢአት ያረጀውን ሰውነት ትተን አዲስ ሕይወት የምናገኝበትን ቀና መንገድ መከተል ይኖርብናል ።

አንዳንድ ሰዎች አሮጌውን ዘመን ሸኝተው አዲሱን ዘመን ለመቀበል የሚዘጋጁት የኃጢአት ሸክማቸ ውን ሳያቃልሉ በኃጢአት ባረጀ ሰውነታቸው ነው ። በኃጢአት ያረጀ ሰውነት ማለትም በዘመን መለወጫ ልዩ ልዩ አምልኮ ባዕድ መፈጸም ነው ።

ቀይ ዶሮ ፤ ገብስማ ዶሮ ፡ ነጭ ዶሮ ፣ ቡሃ በግ ፣ ዳንግሌ በግ ወዘተ ካላረዱ ቆሎውን ቆሉተው በሚዳ ካልበተኑ ቂጣውን ጋግረው ቆራርሰው ካልጣሉ የመሳሰሉትንም ባዕድ አምልኮቶች ካልፈጸሙ ዘመን የተለወጠ የማይመ ስላቸው አንዳንድ ሰዎች ይገኛሉ ። እንደ እነዚህ ያሉት ሰዎች ይህንን አስነዋሪና አሳፋሪ የሆነ ግብራቸውን ከአ ሮጌው ዘመን ጋር የማስወገድ ግዴታ አለባቸው ።

እግዚአብሔር ለሙሴ ከሰጠው ሕግ የመጀመሪያው “ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ በላይ ከሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው ከምድርም በታች በውሃ ካለው ነገር ማናቸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ” የሚለው ነው ኦሪ.ዘጸአት ፳.፫

ይህንን አምላካዊ ትዕዛዝ ባለመገንዘብ ልዩ ልዩ ሟርትን የሚፈጽሙ ሁሉ አድራጐታቸው ተገቢ ስላይ ደለ ከዚህ ተግባር በመከልከል አዲሱን ዘመን በአዲስ መንፈስ መቀበል ይገባቸዋል ። የአምልኮ ባዕድ ርዝራዥ የሆኑ ትን ተግባራት ሳያስወግዱ ወደ አዲሱ ዘመን የሚሸጋገሩ ሰዎች ቢኖሩ ሐዋርያው ጳውሎስ “ሐድሱ መን ፈሰ ልብከሙ” ልቡናችሁን በዕውቀት አድሱ ብሎ ያስተማረውን ቃል ያልሰሙ ናቸው ። የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሁሉ ልቡናውን በዕውቀት ማደስ ይገባዋል በዕውቀት ማደስም ማለት የኃጢአት ምክንያት የሚሆኑትን አምልኮ ባዕዶች ሁሉ ርግፍ አድርጉ ትቶ ሁሉን ለማድረግ የሚችለውን እውነተኛ አምላክ መከተል ነው ። ይኸው ሐዋርያ ለሮሜ ሳዎች በጻፈው መልእክቱ ምዕ. ፲፪.፪ ላይ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህንን ዓለም አትምሰሉት ሲል ተናግሯል ።

ዓለሙ በዕውቀትም ሆነ ያለ ዕውቀት የሚፈጽመውን ምክንያተ ኃጢአት እንዲተውና ሁሉን ማድረግ የሚችለውን እግዚአብሔርን እንዲከተል ለማድረግ ምእመናን ሁሉ ጥሩ ምሳሌ የሆነ ሥነ ምግባር ማሳየት ይኖ ርባቸዋል ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር “መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁም በሰው ፊት ይብራ” ብሏል ማቴ. ፭. ፲፮ ።

በይበልጥ የክርስቶስ ተከታይ ከሆኑት ክርስቲያኖች ጽኑ ሃይማኖት የተወደደ ምግባር ይፈለግባቸዋል ፣ ጨው አልጫ ቢሆን በምን ይጣፍጣል ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደፊት ለምንም አይጠቅምም ተብሎ እንደተጻፈው በክርስቶስ ስም የሚያምኑ ክርስቲያኖች ከአምልኮ ባዕድ ርቀው በሃይማኖታቸው በምግ ራቸው ሌሎችን የሚስቡ ካልሆኑ አማኞች መባላቸው የቀና ትርጉም ሊኖረው አይችልም ።

አሮጌውን ሰውነት ከክፉ ሥራው ጋር ተውት ዕውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳች ሁ ታል ብሎ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደተናገረው አሮጌውን አምልኮ ባዕድ እርግፍ አድርጐ ትቶ እውነተኛውን አዳኝ ክርስቶስን መከተል ያስፈልጋል ።

እግዚአብሔር ቅን ልቡና ትሁት ሰብእና ያላቸውን ሰዎች ጸሎትና መሥዋዕት አምልኮትና ስግደት ይቀ በላል እንጂ በአምልኮ ባዕድ የተመረዘውን ሰው ጸሎትና መሥዋዕት አይቀበልም ። ስለዚህ ከክፉ ሥራ ሰውነታ ችንን በማስወገድ አዲሱን ዘመን ልንቀበለው ይገባናል ይህንንም ለማድረግ ኃያሉ እግዚአብሔር በቸርነቱ ይርዳን ።



www.ethiopianorthodox.org

# የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቃለ ቡራኬ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

በዚህ ዕለት በገጠርም በከተማም ያላችሁ የሀገራችንን ዳር ድንበር ለመ ጠበቅና ለማስከበር በባሕርና በየብስ ያላችሁ ፤ በሕመም ምክንያት በሆስፒ ታል የምትገኙ ምእመናን ሁሉ እግዚአ ብሔር አምላካችን እንኳን ከዘመነ ዮሐንስ ወደ ዘመነ ማቴዎስ በሰላም አደረሳችሁ !



ቅዱስነታቸው በዘመን መለወጫ ቃለ ቡራኬ ሲያስተላልፉ

አእምሩ ከመ በጽሐ ጊዜሁ ለነቂህ እምንዋም ሐለፈ ሌሊት ወመጽአ መዓ ልት ከንዋመ ሐኬት (የምትነቁበት ጊዜ እንደደረሰ ዕወቁ፤ ሌሊቱ አልፎ ቀኑ መጥቶአልና ። (ሮሜ ፲፫፡፲፩) የዘመናት ባለቤት እግዚ አብሔር አምላካችን የቆየውን ዓመት አሳልፎ አዲሱን ዓመት ክረምቱን አስወ ግዶ በጋውን ጨለማውን አርቆ ብርሃ ኑን ስለሚሰጥ በየወቅቱ በየዓመቱና በየዕለቱ አዲስ ምስጋና ሊመሰገን ይገ ባዋል ። የሰው ልጅ ቀናትን አውራኅንና ዓመታትን ቆጥሮና ለክቶ መጠቀም ከጀ መረበት አንስቶ እያንዳንዱ ደቂቃ የታሪክና የሥራ ጊዜ ነው ። ሰው በጊዜ ው ባይሠራበት ጊዜው በሰው ሕይወት ላይ ሥራ ሠርቶ ታሪክ መዝግቦ ያልፋል

እግዚአብሔር መዓልትና ሌሊቱን ፣ በጋና ክረምትን ማፈራረቁ የሰው ልጅ ሥራ ሠርቶ እንዲጠቀምበት ነው ። እንደዚሁም ይህን ከዓመት እስከ ዓመት የማይቋረጠውን የሥነ ፍጥረት ክንውን እየተመለከተ እግዚአብሔርን እንዲያ መሰግን ነው ። እግዚአብሔር በከሃሊ ነቱ ካዘጋጀልን ነገሮች ሁሉ ታላቁ ጊዜ ነው ። ጊዜን የሚመጣጠን ዋጋ የለም ። ስለዚህ ያለፈውን ጊዜ መመለስ የሚ መጣውን ወደ ዛሬ መሳብና በሥልጣን ሥራ መሥራት የምንችለው ዛሬ ባለን በት ጊዜ ነው ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳው ሎስ "ጊዜ ሳለን ለሁሉም መልካም ሥራ እንሥራ" ይላል ። (ገላ ፮ ፣ ፲) በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ምግባረ ወንጌል ለማሳየት ሃይማኖተ ወንጌልን ለመጠበቅ ጊዜው እያንዳንዳችን በሕይ ወት ያለንበት ጊዜ ነው ።"ደስ አያሰ ኙም የምትላቸው ዓመታት ሳይደርሱ ፀሐይና ጨረቃ ሳይጨልሙ ፈጣሪህን አስብ" ተብሎ በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገረው ስለዚህ ነው ።

በየዘመኑ የቆየው ዓመት አለፈ ፣ አዲስ ዓመት ተተካ እያልን እናውጃ ለን ። እንደዚሁም ምዕመናን እርስ በእር ሳቸው እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሳ ችሁ በመባባል መልካም ምኞታቸውን ይገልፃሉ ።

ይሁን እንጂ ፦ ያለፈው ዓመት ለእግ ዚአብሔር ክብር ፣ ለሀገር እድገትና ልማት ፣ ለወገን ብልጽግና የሚሆን ሥራ የሠራንበት ከሆነ ምንጊዜም አዲ ስ ነው እንጂ ያለፈ ዓመት አይባልም ። ነገ የምንቀበለው አዲስ ዓመት ደግሞ



# አክሊለ በረከት

ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን አቡነ ተክ ለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያር ክና የቅዱስ ሲኖዶስ (ሰብሳቢ) ብፁ ዓን ሊቃነ ጳጳሳት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የዚህን በዐል በረከት ለመሳ ተፍ የመጣችሁ ምዕመናን በሙሉ ። ይህን በዓል ለማክበር ያበቃን እግዚ አብሔር የተባረከ ነው ።

ይህ በዓል የቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን የሀገር በዐል ነው ። ለዚህም ም ክንያት አለው ። የኢትዮጵያ ቤተ ክር ስቲያን ጳጳሳትን ከግብጽ እያመጣች የቆየችው በመንግሥቱ ኃይል ነበር ፡ የግብጽ ሡልጣኖችም የግብጽን ጳጳሳት ከኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ጋር የመደራደሪያ መሣሪያ አድርገው ሲጠ ቀሙባቸው ኑረዋል ። ዛሬ ይኸ ሁሉ ችግር ተወግዶ በሀገራችን መሬት ይህ አክሊለ በረከት ከተገኘ ምዕመናን ይህ ን በዐል እልል እያሉ ያከብራሉ ። ሰወ ደፊቱም ቢሆን አንድ ሕዝብ ከዚህ ተ ነስቶ እዚህ ደረሰ መባሉ ስለማይቀር በሀገሩ ውስጥ ያሉት የታሪክ ሁኔታዎች ያለፉትንም ካሉት ጋር አመቻችቶ ማስ ቀመጥ ይጠቅማል ።

ይህ በዓል እኛን ብቻ ሳይሆን ወንድ ሞቻችን አፍሪካውያንን ሁሉ የሚያኮራ በዓል ነው ። በአፍሪካ ውስጥ የፖለቲ ካም ሆነ የሃይማኖት ባዕድ ገዢ ያልደ ፈራት ኢትዮጵያ የአፍሪካውያን ክብር ና ህልውና የተጻፈባት የታሪክ መዝገብ ናትና ።

ይህ በቅዱስ ፓትርያርካችን ራስ ላይ የምናየው አክሊለ በረከት የተገኘው ፣ ይህ ቅዱስ ፓትርያርካችን የተቀመጡ በት መንበረ ፓትርያርክ የተገኘው በቀ ላል ትግል አይደለም አባቶቻችን የተዋ ሕዶ ሃይማኖታቸውን ለመጠበቅና ለት ውልድ ለማውረስ ሳይሰለቹ ከዚህ እስከ ግብፅ ጳጳሳትን ለማምጣት በእግራቸው እየተጓዙ ፣ ለግብጽ ሡልጣ ኖች ማባበያ እየጫኑ አሸዋ ውጦ እያስ ቀራቸው ፡ አውሬ እየበላቸው ፣ ረሀብና ውሀጥም እያሰቃያቸው ፩ሺ፮፻ አንድ ሽህ ስድስት መቶ ዓመት ሙሉ ለሃይማ ኖታቸው ያፈሰሱት ደማቸው በእግዚአ ብሔር የፍርድ ጽዋ ሞልቶ ስለተትረፈ ረፈ ነው ። ይህን አክሊለ በረከትና መን በረ ፓትርያርክ ያስገኘው አባቶቻችን ቶሎ አይሰለቹም ቶሎ አይቆርጡም ፣ መሪዎቹም ቢሆኑ ኢትዮጵያውያን ኤ ጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ ደጋግመው ጠይ ይቀው ነበር ። ነገር ግን በቂ መልስ አላ ገኙም ይሁን እንጂ ተስፋ ባለመቁረጥ አልፎ አልፎም ቢሆን ይህን ጥያቄ አ ልረሱትም ያልተረሳው ጥያቄ ይኸው ዛሬ መልስ አገኘ ።

ይህን በዐል ለማክበር ለማዩትና ለ መደሰት ብዙ አባቶችና እናቶች ተመኝ ተው ነበር ይህ አክሊለ በረከት አንድ ቀን ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጣና ኢ ትዮጵያውያን ክርስቲያኖችም ይህን አክሊል እንደሚቀዳጁ በትንቢት ያው ቁ ነበር ። ነገር ግን አረፍተ ዘመን ገት ቷቸው ይህን አክሊለ ክብር ፡ ይህን መ ንበረ ፓትርያርክ በሩቅ በመንፈስ ተሳ ልመውት አለፉ እንጂ እንደኛ በዐይነ ሥጋ አላዩትም ።

የተከበራችሁ ምእመናን ! በቤተ ክር ስቲያን የሚሰጠው የክህነት ማዕርግ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ይሰጣል ሹመቱም ምእመናንን ወደ እግዚአብ ሔር ለማቅረብ ነው ። ኢትዮጵያ ሀገራ ችን እንኳን መንበረ ፓትርያርክ ሊሰ ጣት ኢትዮጵያዊ ደም ያለው ቆሞስ ኤጲስ ቆጶስ እንዳ ይሆን ታግዶ መኖሩ ብዙ ጊዜ ስለሚነገር ሁላችሁም ታው ቁታላችሁ ይህም እገዳ ከሰው እንጅ ከእግዚአብሔር የመጣ አልነበረም ። በእርግጥ የሰው እገዳ ስንል ዓይነ ልቡና ችን ወደ ግብጽ መመልከት አይቀርም ነገር ግን በውስጥም የርስ በርስ ምቀኝ ነት ነበረበት ። ስለዚህ ካለፈው እየተማ ርን ይህንን መንበራችንን መውደድና ማክበር ይኖርብናል ፤ ሁልጊዜ የሰው ተመልካቾች ሰው የያዘውን አድናቂ ዎች የራሳችንን ግን ናቂዎች እንዳንሆን ነገ ቤተ ክርስቲያንን ለሚረከቡ ልጆች ም ይህን ቀና መንፈስ እናውርሳቸው "ባለቤት የናቀውን ባለ ዕዳ አይቀበለ ውም" እንደሚባለው ታሪክ የሌላቸው ወገኖች ታሪክን ለመመሥረት ሲጣጣ ሩ ፣ እኛ የነበረንንና ያለንን አክብረን ካልያዝነው ሁልጊዜ የሌላው የሚያም ረን ከሆነ ታሪክ የለሾች እንሆናለን ። ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ! "ኢይክል

## ብፁዕ ወቅዱስ ........

ከገጽ ፬ የዞረ

ሥራ የማንሠራበት ፣ መልካም የሥራ ፍሬ የማናሳይበት ፣ ካለፈው ዓመት የበለጠ ሕያው ታሪክ የማንመዘግብበት ፣ በአዲስ ሕይወትም የማንመላለስበት ከሆነ አዲስ መሆኑ ቀርቶ የቆየ ሊሆን ይችላል ። ጊዜን አዲስ የሚያደርገው ሥራ ነው ። መልካም ሥራ የተሠራባ ቸው ጊዜያት ሁሉ ዘወትር በታሪክ ዓምድ አዲስ ሆነው ይኖራሉና ።

ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ከስንፍና የምትነቁበት ጊዜው እንደቀረበ ዕወ ቁ በማለት እንደ አስተማረ በአዲሱ ዓመት ለአዲስ ሥራ በአዲስ መንፈስና ሕይወት መሰለፍ ይኖርብናል ። እንደዚ ሁም ባለፈው ዓመት እግዚአብሔር ያደረ ገልንን መልካም ሥራ ሁሉ እያስታወ ስን በአዲሱ ዓመት ምስጋና ለእግዚአብ ሔር ማቅረብ ይገባናል ።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ለዘአብጽሐነ እስከ ዛቲ ሰዓት (እስከዚች ሰዓት እስከ ዚች ዓመት ላአደረሰን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን ።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ለዘለዓለም ይባርክ



www.ethiopianorthodox.org

ሰብእ ነሚአ ጸጋ ለሊሁ እመ ኢተውህበ ሎቱ እምሰማይ" እግዚአብሔር ሲሰጥ ነው እንጂ ሰው ራሱ ይገባኛል ብሎ በመጓጓትና በመስገብገብ የእግዚአብሔርን ጸጋ አያገኝም ይህንንም ያስተማሩን የቤተ ክርስቲያን አባቶች የታወቁ ። ከእግዚአብሔር የተላኩ የሰጪንና የተቀባዮቹን ምሥጢር የተረዱ ናቸው ። (ዮሐ. ፫ ፡ ፳፯)

በዚች ቅድስት ዕለት ስለ ቅድስናዎ በዐለ ሢመት በቅዱስ ሲኖዶስ ተወከዬ ስናገር የዩሐንስ መጥምቅ ሕይወት ትዝ ይለኛል ፤ ራሱን ደብቆና አዋርዶ በገዳመ ዮርዳኖስ ሲኖር ኢየሱስ ክርስቶስን ለማጥመቅ በራሱ በጌታ ተመርጧል ። ሴቶች ከወለዷቸውም ሁሉ የሚበልጠው የለም ተብሎ በአምላክ ቃል ተመስክሮለታል ። አርአያ ክህነቱና መልክዐ ሕይወቱ ሉቃስ እንደ ገለጠው ለሌላ ያልተሰጠ ነበር ። የቅዱስነትዎም መልክዐ ሕይወት አርአያ ክህነት የሱን ይመስላል ፡ ራስዎን ደብቀው አዋርደው ከሚኖሩበት ገዳም በፈቃደ እግዚአብሔር ተጠርተው እንጂ ይህን አክሊለ በረከት የተቀዳጁት በትረ ክህነቱንም የጨበጡት ሹመት በሚናኝበት በከተማ ኑረው ራስዎን አስተዋውቀው ደጅ ጠንተው አይደለም ። የምናደንቀው ወርቀ ዘቦ ካባ መልበስዎን አይደለም ፤ እንደ አባቶች እንደነ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቄሳርያ ለቤተ ክርስቲያን ክብር ሲሉ ከላይ ወርቅ ቢለብሱ ከውስጥ የለበሱትን ከእግዚአብሔር በቀር ማን ያውቀዋል ? እኛስ የምናደንቀው ከሥራ ወደ ሥራ መሥራትዎንና በክርስቶስ ዐፀደ ወይን በቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖችን እንዲጠብቁ መመረጥዎን ነው ። ይህም የሚያሳየው በቅዱስነትዎና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ምሥጢራዊ ግንኙነት ነው ። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ጥሪ የደረሰዎ በድንገት አልነበረም በእግዚአብሔር ዕቅድ የተጠና ነበር እንጂ፡ ጥሪው እንደደረሰዎ የዮናስን ጉዞ ለመጓዝ አስበው ነበር ። ነገር ግን ዮናስም ድካምን አተረፈ እንጅ ከእግዚአብሔር እጅ እንዳላመለጠ ስለሚያቁት የእግዚአብሔር አገልጋዩ አለሁ አልሸሸሁም እንደ ቃልህ ይሁንልኝ ብለው ተቀብለውታል ። እንዲህ ነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ።

ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን !

እንኳን እግዚአብሔር ሰው እንኳ ባቅሙ ከልቡ ለማያምነው ሰው የቤቱን ቁልፍ አይሰጥም እግዚአብሔር ለቅዱስነትዎ የቤቱን ቁልፍ ያስረከ



ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀ/ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

በው ቢያምንዎት ነው በዚህ ቅዱስ መንበር ቤተ ክርስቲያናችንን እንዲጠብቁ እንዲመግቡና እንዲመሩ ከተሠየሙ ስምንት ዓመታት ሁነዋል ። በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ሐዋርያዊ ተግባሮቹን ፈጽመዋል ። ሃያ አንድ ሊቃነ ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን ቀብተው ሹመዋል ።

በየሀገረ ስብከቱ የሥራ ጉብኝት እያደረጉ መመሪያ ሰጥተዋል ። ዛሬ ካህናቱ የሰበካ ጉባኤን እሸት የሚቀምሱት ቅዱስነትዎ ስለ ሰበካ ጉባኤ መጠናከር ባደረገው ከልብ የመነጨ ድጋፍና ክትትል ነው

ከሀገር ውጭም ቤተ ክርስቲያናችን ድምጿ በበለጠ እንዲሰማ አዳዲስ አህጉረ ስብከቶችን ከፍተው እነዚሁኑ አህጉረ ስብከቶች የሚመሩ ሊቃነ ጳጳሳትን ሾመዋል ።

በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤትና በመላዋ አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ቤተ ክርስቲያናችን የአባልነት መድረኳን ጠብቃ በመብቷ እየተጠመቀች ነው ።

ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችን ስድስት የካህናት ማሠልጠኛዎችን ከፍታ በዓመት ከስድስት መቶ ያላነሱ ካህናትን እያሠለጠነች ታሳማራለች ። ይህ ሁሉ የቅዱስነትዎ ዕድል ነው ።

ቅዱስ አባታችን ለተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ይህን ' ብሊለ በረከትና ቅዱስ መንበረ ፓትርያርክ ለማምጣት ሲታገሉ ሕይወታቸውን ያሳለፉ አባቶቻችንን ነፍሳቸውን ይማር እያልን በዚች ቅድስት ዕለት እንድናስታውሳቸው የቅዱስነትዎ ፈቃድ ይሁንልን ።

ለቅዱስ ስሙ ተጨማሪ ሥራ አስፋፍተው እንዲሰለፉለት የማያልቅበት አምላክ ረጅም ዕድሜና ጤንነት ይስጥልን ።

ወይትባረክ እግዚአብሔር
አባ ጎርጎርዮስ
የሸዋ ሊቀ ጳጳስ



# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ከብፁዕ አቡነ ገርማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሱዳን ሊቀ ጳጳስና የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተ/ዋና ጸሐፊ

ካለፈው የቀጠለ ።

በሚኒ ፕሮጀክት አቋም አንፃር የተሰጠ ርዳታ ድምር 203.524 ብር ከ10 ሳንቲም ፤ መመሪያችን ከፍ ብሎ በዝርዝር ለተጠቀሱት አህጉረ ስብከት እ.ኦ.ዘ.አ. በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም የበጀት ዘመን በድምሩ ሁለት መቶ ሦስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ አራት ብር ከአሥር ሣንቲም ያበረከተበት ዓይነተኛ ምክንያት ፡ በእነዚሁ ክፍላተ ሀገር በሚገኙት አድባራትና ገዳማት ያሉት ካህናት በጠባብ ኑሮ ተወስነው ከመኖር አልፈው ፤ ከፍ ብሎ ከሀ እስከ ረ ፊደላት በተመለከቱት የልማት ሥራዎች በትርፍ ሰዓታቸው ወይም በወር ተራ እየተሰማሩ ከሚያገኙት ምርት ወይም ውጤት አንጻር የዕለት ኑሮአቸውን እንዲያሻሽሉና በአካባቢያቸውም ለሚገኙት ምዕመናን የልዩ ልዩ ሥራ ክቡርነትንና ጠቃሚነትን ይበልጥ እንዲያስተዋውቁ ጭምር እንዲረዳ አርቆ በማሰብ ነው ።

ይሁን እንጂ ከሚኒ ፕሮጀክት አንጻር እ.ኤ.ዘ.አ. በ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. የተሰጠውን የገንዘብ እርዳታ ከ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ጋር በሂሳብ ስሌት መልክ ስናነጻጽረው በ፲፱፻፹፬ ዓ.ም የተሰጠው የኢት ብር ፩፻፺፯ሺ.፶፻፸፯. ፴ ሲሆን በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም ደግሞ ብር ፪፻፫ሺ.፭፻፳፬.፲ሣ ነው ልዩነት በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. የበጀት ዘመን ለልዩ ልዩ አህጉረ ስብከት የሰጠነው የእርዳታ ገንዘብ ብር ፺፮ሺ.፰፻፵፯.፸ (ዘጠና ስድስት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ሰባት ብር ከሰባ ሳንቲም ወይም በመቶ ፩፻ ፺.፸፰) የበለጠ መሆኑ ግልጽ ነው ።

በገንዘቡም አሰጣጥ ረገድ በመምርያችን ሂሳብ ክፍል የተዘጋጀ ቁጥር ፩ የሂሣብ ሠንጠረዥና እንዲሁም በእህል በልብስና በመሳሰለው ደግሞ ከማስተባበሪያ ክፍላችን የቀረበ ቁጥር ፪ መግለጫ ከዚሁ ጋር በአባሪነት ይገኛሉ ።

ከፍ ብሎ በተካሄደው ገለጻ በአንድ የሳበካ ጉባኤ አካባቢ የሚገኙት ካህናት በአባልነት በመደራጀትና በአንድ ዓላማ ሥር ተሰብስበው በዕለታዊ ኑሮ ረገድ የሚገጥማቸው ችግር ቢኖር በኅብረት ሠርተው በማግኘት ችግራቸውን አስወግደው በመንፈሳዊና በማኅበራዊ ሁሉ ተባብረው ራሳቸውን በራሳቸው በመርዳት ራስ አገዝ ሕይወታዊ ኑሮ ለመኖር እንደሚያስችላቸው ይገመታል።

ይህን በመሳሰለው አጋጣሚም እነዚህ ካህናት ለምዕመናኑ መልካም አርአያ በመሆን ምሳሌነትንም በቀደምትነት እንደሚያተርፉ ይጠበቃል ።

ከዚህ ከፍብሎ ከ፩ እስከ ፲፩ ተራ ቁጥሮች ድረስ ለተጠቀሱት አህጉረ ስብከት በልማት ረገድ በበኩላችን ለአደረግነው የገንዘብ እርዳታ በአንፃሩ ስለተገኙት ልዩ ልዩ ውጤቶች ጉዳዩ በቅርብ ይበልጥ ከሚመለከታቸው አህጉረ ስብከት ሰፋ ያለ መግለጫና መረጃ እንደሚሰጥ ይጠብቃል ።

## ለችግር ማስወገጃ ስለተ ሰጠው የገንዘብ እርዳታ

እንደሚታወቀው ፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ልምላሜዋ የታወቀች ለመሆኗ ብዙ የውጭ ሀገር ታሪክ ጸሐፊዎች በስነ ጽሑፋቸው መስክረውላታል

ሆኖም ጊዜ አልፎ ጊዜ ሲተካ ፤ የተፈጥሮ ሀብት ከሆኑት አንዳንድ ነገሮች ይኸውም እንደ ዛፎች የመሳሰሉት እየተጨፈጨፉ በመመንመናቸው ፡ ምድሪቱም በዝናም እጥረት ምክንያት የምታበረክተው ልዩ ልዩ ሰብል በዚሁ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያቆለቆለ በመሄዱ የድርቁ ሁኔታ አልተሻሻለም ።

በዚሁ መንሥኤ በአንዳንድ ክፍላተ ሀገር አልፎ አልፎ የእህል እጥረት በመድረሱ ፤ በእህልና በልብስ ስጦታ ረገድ በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያችን በኩል የተበረከተውን ወደፊት በሰንጠረዥ እንገልጻለን ።

ሆኖም በገንዘብ አሰጣጥ ረገድ አባሪው ቁጥር ፩ የሂሳብ ሠንጠረዥ በአጠቃላይ እንደሚያመለክተው ፡ ድምር ፰፻፹፱ሺ.፫፻፷፪. ፺፩ ተሰጥቷል ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሁሉ ፤ የልማትና ክርስቲያናዊየበጎ አድራጊ ድርጅቶች ጋር በሚያደርገው መቀራረብ ፤ በሀገራችን አልፎ አልፎ የደረሰውን የድርቅ ሁኔታ ለእነዚሁ ድርጅቶች በየጊዜው እንዲረዱ በማድረግ የአገኘው የገንዘብ እርዳታ ከፍተኛውን ድርሻ ከዚሕ በላይ ከቁጥር ፩ እስከ ፬ ለተመለከቱት አህጉረ ስብከት እ.ኤ.ዘ.አ. በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. የገንዘብ እርዳታ ያበረከተ ከመሆኑም ባሻገር ፤ ለወደፊቱ የየሀገረ ስብከቱን በተጨባጭና በበቂ ማስረጃዎች ድጋፍ ያላቸውን የተሟላ ወቅታዊ መጠይቆች በጥሞና ተቀብሎ በማጤን ቅደም ተከተሉንም በመጠበቅና ይልቁንም ለአሳሳቢነቱ ሁኔታ ሚዛናዊ ትኩረት በመስጠት አቅም በፈቀደ መጠን በቆመለት ዓላማ አንፃር በሰብአዊ ተግባር አፈጻጸም ረገድ የእርዳታ እጁን በቅን መንፈስ ከመሰንዘር እንደ ማይቆጥብ በዚህ አጋጣሚ በቅድሚያ ላረጋግጥ እወዳለሁ ።

ከዚህም አኳያ ከዚህ በላይ ከ፩ እስከ ፲፬ ተራ ቁጥሮች እንደተመለከተው ፡ ድርቅ ለአጠቃቸው ክፍላተ ሀገር እ.ኤ.ዘ.አ በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ብቻ ለችግር ማስወገጃና ለልዩ ልዩ በጠቅላላው ብር ፰፻፹፱ሺ.፫፻፷፪. ፺፩) (ስምንት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከዘጠና አንድ ሣንቲም) በየአህጉረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት አማካይነት እንዲከፋፈል አድርገናል ።



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ረገድ እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፹፪ ዓ.ም. ለተለያዩ ክፍላተ ሀገር ለድርቅ ብር ፰፻፴፯ሺ.፭፻፲፫.፰፰ ለልዩ ልዩ ወጭዎች ብር ፻፰፻፴ሺ.፱፻፹.፲፰ በድምሩ ብር ፪፻፳፰ሺ.፱፻፺፫.፹፫ (ሁለት መቶ ሃያ ስምንት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሦስት ብር ከሰማኒያ ሦስት ሣንቲም) ወጭ በማድረግ ረድተናል።

በሂሳብ ስሌት ረገድ እ.ኤ.ዘ.አ. በ፲፱፻፹፪ ዓ.ም. የከፈልነውና በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ለችግር ማስወገጃና ለልዩ ልዩ ክ ስጠነው ብር ፰፻፹፱ሺ.፫፻፸፪.፺፩ (ስምንት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺህ ሦስት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከዘጠና አንድ ሳንቲም) ጋር ሲመዛዘን እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ብር ፮፻፷ሺ.፫፻፸፱.፴፰ (ስድስት መቶ ስድሳ ሦስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ብር ከስምንት ሣንቲም (ወይም በመቶ ፫፻፹፰.፫) እ.ኤ.አ.ዜ በ፲፱፻፹፫ የበጀት ዘመን በብልጫ የእርዳታ ገንዘብ ለተለያዩ አህጉረ ስብከት አበርክተናል ማለት ነው። ይኸውም የእህልን ፣ የፋፋን ፣ የብርድ ልብስንና የመሳሰለውን ሳይጨምር ነው።

## ለሰበካ ጉባኤ አስተዳደር መምሪያ የበጀት ክፍያ ፡-

የቅድስት ቤተክርስቲያናችንን አንድነትና አስተዳደር በሥነ ሥርዓት መርቶ ለማጠናከር ይቻል ዘንድ ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፣ በቃለ አዋዲው ስለሰበካ መንፈስዊ ጉባኤ በሰኔ ወር ፲፱፻፸፩ ዓ.ም. የማሻሻያ ደንብ ማውጣቱ ይታወሳል።

በአዲሱ ደንብ መሠረት ፣ በአዲስ አበባ ከተማና በሌሎችም አህጉረ ስብከት የሰበካ ጉባኤ በሰፊው በመቋቋም ላይ ስለሚገኝ ፣ የቤተክርስቲያናችን የልማት እድገት ከመቼውም ይልቅ እየዳበረ በመንገዝ ላይ ይገኛል።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ... ድሞ ካህናቱ በመጠነኛ በጀት ይተዳ... እንደነበር ቢታወስም በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማና በአህጉረ ስብከት ደረጃ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የሰበካ ጉባኤ በማቋቋም ምዕመናኑን በማሰባሰብ ፣ የየቤተክርስቲያኑ ካህናት ፣ ዲያቆናትና ሌሎችም አገልጋዮች የሚተዳደሩበትን ገንዘብ በየዓመቱ ምዕመናኑ በነፍስ ወከፍ በመጠኑ እንዲያዋጡ በማድረግ በሰባካ ጉባኤ ለተመዘገቡት ምዕመናን ነፃ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

ይሁን እንጂ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ መምሪያ በማሻሻያው ደንብ መሠረት የሰበካ ጉባኤዎች በሚገባ የተቋቋሙና በቃለ አዋዲው መሠረት ዓላማውና ተግባሩ በሚገባ የሚራመድ መሆኑን በዘመቻ መልክ ቡድን እየላከ በቅርብ የሚቆጣጠርና በመምሪያውና በአህጉረ ስብከት ደረጃ እንደአስፈላጊነቱ ሰሚናሮችንም ጭምር እያካሄደ በመሆኑ ፣ በአባሪው የሂሳብ ሠንጠረዥ ቁጥር እንደተመለከተው ፣ እ.ኤ.አ.ዘ. በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ለሰበካ ጉባኤ አስተዳደር መምሪያ በበጀት መልክ የኢት ብር ፩፻፷፬ሺ.፯፻፹፯.፶፩ (አንድ መቶ ስድሳ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሰማኒያ ስድስት ብር ከሃምሣ አራት ሣንቲም) የከፈልን ሲሆን እ.ኤ.ዘ.አ. እስከ ፲፱፻፹፪ ዓ.ም ድረስ ያለው ሂሳብ ለተመረመረበት ደግሞ ብር ፫ሺ.፯፻፴፰.00 ለኦዲተሮች ወጭ በመደረጉ እ.ኤ.ዘ.አ. በ፲፱፻፹፫ የበጀት ዘመን ለዚሁ መምሪያ ወጭ ያደረግነው በድምሩ የኢት/ብር ፩፻፷፰.ሺህ ፭፻፳፭.፶፩ (አንድ መቶ ስድሳ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ሃያ አንድ ብር ከአምሳ አራት ሣንቲም) በተመሳሳይ ወራት በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. በከፈልነው ብር ፩፻፴፰ሺ.፱፻፳ ጋር ሲነጻጸር ፣ በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. የከፈልናቸው ብር ፴፱ሺ.፭፻፩.፶፩ ወይም በመቶ ፩፻፳፫.፯፰ ብልጫ አሳይቷል።

## ስለሰንበት ትምህርት ቤት የበጀት አከፋፈል ፣

እንደሚታወቀው በአዲስ አበባ አካባቢና በአህጉረ ስብከት ደረጃም የሰንበት ትምህርት ቤት መሠረታዊ አቋም፡ ሕፃናትም ሆኑ ወጣቶች በቤተክርስቲያናችን ሥርዓትንና ሕግን እየተማሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ በመሆን ፣ በመንፈሳዊውና በሥጋዊው ትምህርት ተኰትኩተውና ታንጸው ሀገርንና ወገንን በቀና ሕሊና እንዲያገለግሉ ለማድረግ ነው።

ይህም ግቡን ሊመታ የሚችለው አባቶችና እናቶች አቅም በፈቀደ መጠን ፣ ልጆቻቸውንና በአጠቃላይ አነጋገርም ወገኖቻችን መንፈሳዊ ትምህርት ጭምር እንዲገበዩ ፣ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሲያበረክቱ መሆኑ ግልጽ ነው። የሰንበት ትምህርት ቤት ከጥቅምት ፲፯ እስከ ጥቅምት ፲፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ድረስ የሰንበት ት ቤትን በሚመለከት ሰሚናር አድርጓል።

ሆኖም የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ እ.አ.ዘ.አ. በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. በበጀት መልክ ብር ፳፰ሺ.፲፩.፰ (ሃያ ስምንት ሺህ አሥራ አንድ ብር ከስድሳ ሣንቲም) ለሰንበት ትምህርት ቤት የከፈለ ሲሆን ቀደም ሲል ለተፈጸመው ሂሳብ ምርመራ ደግሞ ብር ፭፻ (አምስት መቶ ብር) ከፍላ ል።

የሰንበት ትምህርት ቤት እ.አ.ዘ.አ. የ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. በጀት ከቀድሞ ይልቅ ከፍ እንዲል በጥር ወር ፲፱፻፸፯ ዓ.ም በመሥሪያ ቤታችን በተካሄደው የኮንሰርሽየም ስብሰባ መምሪያችን ባደረገው ጥረት በእርዳታ ሰጭዎች ዘንድ ተቀባይነትን በማግኘት ፍሬያማ ሆኗል ከመባል ደረጃ ደርሷል።

ይቀጥላል



# አብሮ የበላን ቅዱስ ዮሐንስ አይሽረውም

ቅዱስ ዮሐንስ ዘመን መለወጫ እንደመሆኑ መጠን በሕብረተሰቡ ዘንድ ተወዳጅነትና ተናፋቂነት ያለው ታላቅ በዓል ነው። በመሆኑም ትልቁም ሆነ ትንሹ በጠቅላላ ሁሉም በየበኩሉ ሰፋ ያለ ዝግጅት ያደርጋል ሕፃናቱ ጉንጉን አበባ ሰርተው ከወላጆቻቸው ቡራኬ ያገኛሉ። ማንኛውም ሕብረተሰብ ደግሞ ቤቱ በፈቀደለት መጠን ድግስ ደግሶ ቄጤማ ጐዝጉዞ ጎረቤት ከጎረቤቱ አካባቢ ከአካባቢ ጋር ምሣና እራት እየተገባበዘ እየበላ በዓሉን ያከብራል። አብሮ የበላን ቅዱስ ዮሐንስ አይሽረውም የተባለው ስለዚህ ነው።

በዚህ አነጋገር አባቶቻችን ሲጠቀሙበት ኑረዋል። ሩሶ የተባለው የፈረንሣይ ሊቅ "የብዙዎችን ጥቅም በግል ጥቅም ከመለወጥ የበለጠ አደገኛ ነገር የለም" በማለት አስተያየቱን ደግፎታል። ይህን የተገነዘቡ የቀድሞ አባቶቻችን ያገኙትን አብሮ መብላት ፣ አብሮ መጠጣት ፣ ከሰው ጋር አብሮ መኖር ይወዱ ነበር። በይበልጥም አገራቸን እንግዳ ተቀባይ ሲያሰኟት የኖሩት አላፊ አግዳሚውን ወጭ ወራጁን ከቤታቸው ተቀብለው አብልተው አጠጥተው ፣ እግሩን አጥበው አልጋቸውን ለቀው አስተኝተው እነሱ በምድር ላይ ተኝተው ሲነጋ ስንቁን ሰጥተው መንገድ አሳይተው እንግዳውን ይሸኙ ስለነበር ነው።

በጣም የሚያስገርመው ደግሞ ሁሉም ተባብረው ትንሽ ትልቅ ሳይባባሉ ድሀ ሀብታም በማለት ሳይለያዩ አብረው በልተው አብረው ጠጥተው አብረው ሠርተው አብረው ተጫውተው ደስታውንም ሆነ መከራውን አብረው ተካፍለው ለሌላውም ጥሩ ምሳሌ ሆነው ከመኖራቸውም ሌላ እንደ ዘመን መለወጫና እንደ መስቀል ባሉት በዓላት እየተጠራሩ አንድ ላይ ይገባበዙ ነበር። ስለዚህ በመካከላቸው የሚፈጽሙትን መልካም አድራጎትና አብሮ መብላት ቅዱስ ዮሐንስ አይሽረውም የተባለው ከዚህ የተነሳ ነው።

በዚህ አኳኋን መከራ ቢመጣና አደጋ ቢነሳ ሁሉም ተካፋይ ይሆናል እንጂ አንዱ ሌላውን ለመከራ አሳልፎ አይሰጥም አንዱ ሲሰቃይ ሌላው ዝም ብሎ አይመለከትም ምክንያቱም ደስታም ከሆነ የሁሉ ደስታ ነው መከራም ከሆነ የሁሉ መከራ ነውና። ቶማስ አኲይናስ የተባለው ሊቅ የሰው ሐብቱ የጋራ እንጅ የግሉ እንዳልሆነ በመቁጠር ከችግረኞች ወገኖቹ ጋር ያለማመንታት ተካፍሎ ሊጠቀምበት ይገባዋል ብሏል። እንዳለውም ኑሮ የጋራ እንጂ የግል አይደለም መማርና ማስተማር ሌላውን ለማገልገል እንጂ ራስን ለማገልገል አይደለም መኖርም መማርም ደስ የሚያሰኘው ደስታውንም ችግሩንም ከወገን ጋር አብረው የተካፈሉት እንደሆነ ነው። ምክንያቱም በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ የግል የሆነ ነገር የለምና ነው ያገኙትን ከወገን ጋር ተካፍሎ ከበሉ ፣ አብሮ የበላን ቅዱስ ዮሐንስ አይሽረውም ያሉትን የአባቶቻችን ምሣሌ በሥራ መተርጐም ነው።

በዘመናችንም ቢሆን አሁን ያለው ህብረተሰብ ከአባቶቹ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ይህን የተቀደሰ መንፈሳዊ ባህል ተከትሎ አሮጌውን ዘመን ይሸኛል አዲስ የሆነውን ዓመት ቅዱስ ዮሐንስን በአበባ ይቀበላል ቤቱን በቄጤማ ጐዝጉዞ ሁሉን ነገር አዘጋጅቶ ያከብረዋል አከባበሩ በዚህ ብቻ ሳይወሰን እርስ በርስ ከባበሩ በዚህ ብቻ ሳይወሰን እርስ በርስ በመጠያየቅ ጎረቤት ከጎረቤቱ ፣ ወዳጅ ከወዳጁ ፣ አካባቢ ከአካባቢ ጋር እየተጠራራ አብሮ በመብላትና በመገባበዝ የደስታውና የበዓሉ ተካፋይ በመሆን ቅዱስ ዮሐንስን ወይም ዘመን መለወጫን ያከብረዋል ተፋቅሮና ተባብሮ በአንድነት የሚበላ እንዲህ ያለ ኅብረተሰብ በደስታ ጊዜ እንደማይለያይ ሁሉ መከራም ችግርም ቢመጣበት ተባብሮ ችግሩን ያስወግዳል ጠላትም ቢመጣበት ተባብሮ ድል ይነሳል በልማትም በእድገትም በእምነትም ጠንካራነቱን ያስመሰክራል።

ከወገን ጋር መብላት ደስ የሚላቸው እንዳሉ ሁሉ ለብቻ መብላት ደግሞ የሚያስደስታቸው በቀድሞም ዘመን እንደነበሩ በጊዜያችንም አልፎ አልፎ አንዳንድ አይጠፉም የቀድሞዎቹን ከሕብረተሰብ ታሪክ ለመረዳት ይቻላል የአሁኖቹን ደግሞ በየጊዜው እነገሌ ይህን ያህል ገንዘብ አጠፉ እነገሌ ታማኝነታቸውን አጎደሉ እየተባለ በመገናኛ ሲነገር እንሰማለን እንዲህ ያሉት ሰዎች ወደንዲህ ያለ ተግባር ሊሰማሩ የሚችሉ ከሀገር እድገት ይልቅ የራሳቸውን ዕድገት ከወገን ፍቅር ይልቅ ራሳቸውን አብልጠው ስለሚወዱ ነው ይህም ብቻ አይደለም እናት አባታቸው የሞተባቸውን ከማሳደግ ይልቅ ገንዘባቸውን ማባከን ደስ ይላቸዋል። ከድሆች ጋር ከመብላት ይልቅ ለብቻ መብላት ያረካቸዋል እንዲህ ያሉት ሰዎች ብቻቸውን ስለበሉ መከራ ባጋጠማቸው ጊዜ የመከራውን ጽዋ ብቻቸውን ከመጨለጥ በቀር ተካፋይ የላቸውም። ይህንንም መጥፎ ተግባር በመፈጸማቸው ስለሚጋለጡ ቅዱስ ዮሐንስን ሳይውሉ መስቀልንም ሳይተኩሱ የሚገባቸውን የፍርድ ዋጋ ያገኛሉ። ይህም ሊሆን የሚችለው እራስን ከመውደድ የተነሳ ነው።

አብሮ የመብላትን ነገር ካነሳን ዘንድ ቅዱስ ዮሐንስን ተጠግተው በሚመጡ በአጉል ባህሎች አማካኝነት የሚዘጋጁ ምግቦች አሉ። እነሱም ለሚርት ፣ ለአቴቴ ፣ ለአድባር እነዚህን ለመሳሰሉት ነው። ከምግቦቹ አይነት ጥቂቶቹን ብንጠቅስ በርከት ያለ ገብስ ይሸመትና ተከክቶ ለቅንጬ ይዘጋጃል ግማሹ ለቦርዴ ይሆናል መልክ ያላቸው እንስሳት



www.ethiopianorthodox.org

ይገዛሉ በርከት ያለ ቡና ይገዛል ። ከቅዱስ ዮሐንስ ዋዜማ ጀምሮ እስከ ሦስት ቀን ድረስ ቅንጨው እየተቀቀለ ቅቤ እየተንጣለለበት ቡና በብዛት እየፈላ የእንስሳቱ ሥጋ እየተጠበሰ ሰው በብዛት እየተጠራ ሲጋበዝ ይሰነብታል እንዲህ ያለው አብሮ መብላት ቅዱስ ዮሐንስ አይሽረውም የሚለውን አይመለከትም ምክንያቱም የተፋት ነገሮችን ስለሚያስከትል ነው ።

አንደኛ አጉል ባህል በመሆኑ ሁለተኛ ፀረ-ህብረተሰብ ሆኖ በመገኘቱ ሦስተኛ ( አምልኮትን የሚቃወም በመሆኑ አራተኛ ታላቅ የወር ወጪን በመቀነስ በቤትሰብ ላይ ታላቅ ችግርን እያመጣ በመካከል ታላቅ ጭቅጭቅን ስለሚፈጥር ከእንዲህ ያለው ምግብ መሳተፍ አያስፈልግም ። ይህን ያልነበት እንዲህ ያለው አጉል ባህል ከመልካሙ ባህል ጋር አብሮ በቀል ሆኖ ከመታየቱ በፊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የወንጌል ስምሪት ዘመቻ በማድረግ ከሥሩ ነቅላ ማጥፋት ይገባታል ። የሚመለካታቸውም ድርጅቶች ሁሉ ተባባሪ ሊሆኑ ይገባል ።

እንግዲህ የሰው ልጅ አብሮ መብላትም ሆነ መሥራት ደስ የሚለው አሮጌውን ዘመን በአዲሱ ዘመን እንደለወጠ ሁሉ ህይወቱንም በመንፈስ ሲያድስና በሥራ ሲለውጥ ነው ። ይህን ካደረገ ሁሉ ነገር አዲስ ይሆለታል የሠራው ሁሉ በረከት ያገኛል ። ይህንንም የሚያረጋግጠው አሪት ዘዳግም ምዕራፍ ፳፰ ከቁጥር ፪-፰ የሚከተለውን ይናገራል ። "የአምላክህንም ቃል ብትሰማ እነዚህ በረከቶች ሁሉ ይመጡልሃል አንተ ብሩክ ትሆናለህ በእርሻህም የተባረከ ትሆናለህ የምድርህም ፍሬ የላምህም ርቢ ፣ የበግህም ርቢ ብሩክ ይሆናል። እንቅብህና ቡሃቃህ ብሩክ ይሆናል ። አንተም በመግባትህ ብሩክ ትሆናለህ፣ በመውጣትህም ብሩክ ትሆናለህ ።

እግዚአብሔር በላይህ የሚቆሙትን ጠላቶችህን በፊትህ የተመቱ ያደርጋቸዋል ። በአንድ መንገድ ይመጡብሃል በሰባትም መንገድ ከፊትህ ይሸሻሉ ።የእግዚአብሔር በረከቱ በአንተ ላይ በጐተራህ በእጅህም ሥራ ሁሉ እንዲወርድ ያዝዛል ፣ አምላክህ እግዚአብሔር በሚሰጥህም ምድር ይባርክሃል" እንዳለውም ተፋቅሮ የሚበላን ሕዝብ ቅዱስ ዮሐንስ አይሽረውም ተባብሮ የሚኖርና ጠንክሮ የሚሰራ ህዝብም ይህን የመሰለ በረከትን ያገኛል የሚሠራ ኃይሉን ያድሳ ተብሏልና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



# ሥዕለ ማርያም በዼዴንያ

ጼዴንያ በምትባለው አገር በሃይማኖት የጸናች በምግባር የቀናች ማርታ የምትባል አንዲት ሀብታም ሴት ነበረች ፣ እሷም ከዕለታት አንድ ቀን ፣ በልቧ የዚህ ዓለም ገንዘብ ፡ ሀብቱ ንብረቱ አላፊ ጠፊ ከንቱ መሆኑን አስባ ፣ ጌታ በወንጌል የተናገረውን ቃል ተገንዝባ እንዲህ አለች ጌታ ሰውን ነፍሱን ቤዛ ካልሰጠ ዓለሙን ሁሉ ቢገዛ ቢነዳ ቢያተርፍ በነፍሱ ከተጐዳ ምን ይረባዋል ምን ይጠቅመዋል ። ብሏል ብላ ማር ፰ ቁ. ፴፮ ተመ/ እኔስ ለነፍሴ መዳኛ ለሥጋዬ መጠገኛ መልካም ሥራ ካልሠራሁላት ምን ይረባኛል ምን ይጠቅመኛል ብላ ፣ በገንዘቧ መልካም ሥራ ልትሠራበት አሰበች ፣ አስባም አልቀረች ፡ እንዲህ አለች ፡ አብርሃም እንግዳ በመቀበሉ ሥላሴን አቤቱ ተቀብሎ ለማስተናገድ በቃ ደግሞም 2ተኛ እንደዚሁ ሁሉ ፣ ሎጥ እንግዳ መቀበል በመውደዱ ሁለት የመላእክት አለቆችን ተቀብሎ በቤቱ ውስጥ አሣደረ ። 3ተኛም የአልዓዛር እኅት ማርታም የሴት ባልትና በማወቋ ፣ እንግዳ በመቀበሏና ሐዋርያትን በማስተናገዷ በጣም ትደከም ነበረችና እኔም እንደ እሷ ለመልካም ሥራ እንግዳ ለመቀበል ልድከም ብላ የእነዚህን የ፫ቱን ሰዎች ሥራዎች ከሁሉ እንዲበልጡ አውቃና ተገንዝባ ሠፊ የእንግዳ ማደሪያና መቀበያ ትልቅ አዳራሽ አሠራችና እንግዶችን እየተቀበለች ታስተናግድ ጀመር እነሱም ከበሉና ከጠጡ በኋላ ነገረ መለኮትንና የቀደሙ አባቶችን ታሪክና ነገር ትጠይቃቸው ነበር ። ከዕለታት ፩ ቀን ብዙ እንግዶች ተሰብስበው ለማደር ወደ ቤቷ መጡ ፣ እሷም እንደልማዷ የሚጠቅማትን ነገር ጠየቀቻቸው ፣ እነሱም እንዲህ አሏት በኢየሩሳሌም የእመቤታችንን ሥዕል ጥሩ እያደረጉ የሚሥሉ ሠዓሊዎች እንዳሉ ነገሯት ። ማርታም ይኸን ሰምታ ከእመቤታችን ፍቅር የተነሣ ልቧ እንደ እሳት ነደደ) ።

እሷም እባካችሁ ከእናንተ ወደ ኢየሩሳሌም የሚሄድ ገንዘብ የምሰጠው ፡ ሥዕል ገዝቶ የሚያመጣልኝ አለን ብላ

ካንች እቀበላለሁ አላት እሷም ደስ ብሏት ከጫማው ላይ ወድቃ እግሩን እየሳመች እንግዲህ አደራ ብላ አማጠነችው አደራ ጥብቅ ፣ ሰማይ ዕሩቅ ነውና እሱም ማልዶ ጧት ተነሥቶ ገሥግሶ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ከዚያም የሔደበትን



ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ

በኃዘንና በልቅሶ ጠየቀቻቸው ። ከእነዚያ መካከል አንዱ መነኩሴ እኔ እሔዳለሁና በገንዘቤ ገዝቼ አመጣልሻለሁ በኋላ ስመለስ የገዛሁበትን ገንዘብ

ሥራ ከፈጸመ በኋላ ማርታ እንዲገዛላት አደራ ያለችውን አስቦ መልኳ ያማረ ጥሩ ሥዕል ገዛላት ፣ ይህችውም ሥዕል



www.ethiopianorthodox.org

ወንጌላዊው ሉቃስ የሣላት ናት ትባላ
ለች ።
ያም መነኩሴ ሥዕሊቱን ይዞ ለጊዜ
ው ወደ ጴጌንያ በሚወስደው መንገድ
ተ፡3ዘ ሲሄድ አንበሳ ሊበላው እየጮኸ
አፉን ከፍቶ መጣበት ፤ ያም መነኩሴ
ከአንበሳው ግርማ የተነሣ ደንግጦ ይን
ቀጠቀጥና ይርበተበት ጀመረ ። በዚሁ
ደንግጦ ቆሞ ሳለ ፤ ያች የያዛት ሥዕል
ከአንበሳ ጩኸት ፯ እጅ በሚበልጥ ጩ
ኸት ተናገረች ፤ ያም አንበሳ የሥዕሊቱ
ን ድምፅ ሰምቶ ደንግጦ ፈጥኖ ሸሸ ።
ያም መነኩሴ የሥዕሊቱን የጩኸት ድ
ምፅ ሰምቶ እያደነቀ ሄዶ ፪ተኛም መን
ገደኛውን ሁሉ መቀማትና መግደል ል
ማዳቸው የሆነ የበረኻ ሽፍቶች አገኙት
ቁም ብለው ከበውት ሊበረብሩት በያ
ዙት ጊዜ ከላይ እንደ ገለጥነው ያች ሥ
ዕል እንደ መብረቅ ጮሐ በታላቅ ቃል
ተናገረች ።
እነዚያም ሼፍቶች ፈርተው ይህ ጩ
ኸት ከየትም እንደሆነ ሳያውቁ ደንግጠ
ው ሸሹ ። ያም መነኩሴ እነዚህ» ፪ት
የሚያስደንቁ ታምራቶችን በሰማና ባዩ

ጊዜ በልቡ ክፉት አሰበ ። አስቦም አ
ልቀረ ፤ እንዲህ አለ ። እነዚህን ፪ት ታ
ምራቶች ስታደርግ እንዳየኋት ሁሉ ለኔ

ም ታደርግልኛለች ረዳት እንድትሆነኝ
ወደ አገሬ ወደ ኢትዮጵያ ይዣት እሔ
ዳለሁ ብሎ ክዳት አሰበ ይህች ሥዕል
በፍጹም ልቡናዋ ከምትወዳት ሴት
ከማርታ ጋራ እንድትኖር በገዛ ፈቃ
ዷ እንደ መጣች አላወቀም ። እሱ ግን
የመሰለው ለነጋዴ እንደሚሸጠው ሸቀ
ጥ ያለ ፈቃዷ በግድ በገንዘቡ ገዝቶ ያ
መጣት መስሎት ነበር ስለዚህ እሱም
እንግዲህ ለዚች ሴት አልሰጣትም ከ
ድቼ ባገሬ መንገድ እሔዳለሁ እንጅ
ወደ እሷ ቤት በሚወስደው መንገድ አ
ልሔድም አለ እንዲህ እያለ ሲያስብና
በልቡ ሲያወጣ ሲያወርድና ሲመክር ከ
ባሕሩ ዳር ደረሰ ከዚያም ብዙ መርከቦ
ች ከወደባቸው ቆመው አገኘና ባለ መ
ርከቦችን ከዚህ ተነሥታችሁ በየትኛው
መንገድ ትወጣላችሁ አላቸው ። አንዱ


ጴጄንያ ወደ ሚባለው አገር ነው አለ
ው ። መልካም ብሎ በዚያች መርከብ
ተሣፍሮ ሲሄድ አውሎ ነፋስ ተነሣበት
ና ያለፈቃዱ እየነዳ ወደ ጴጄንያ በሚ
ያወጣው ወደብ ወሰደው ። ያለ ፈቃዱ
በግድ ወስዶታልና በልቡ እንዲህ ብሎ
ተንኰል አሰበ አስቦም አልቀረ ያች ሥ
ዕል ግዛልኝ ብላ ያማጠነችኝ ሴት እኔ
ማን እንደሆንኩ አታውቀኝምና ብሎ
ወደ ማርታ ቤት ሄዶ ! መንገደኛው እን
ግዳ በጣም ብዙ ነበርና ወደቤቷ ገብቶ
ከመንገደኞቹ ጋራ እራቱን በልቶ አደ
ረና ሲነጋ ከእነሱ ጋራ ወደ ውጭ ወጥ
ቶ ሊሄድ ካጥሩ በር ደረሰ እነሱ ወጥተ
ው ሲሄዱ ፣ እሱ ግን በሩን ወጥቶ መሔ
ድ ተሣነው የማርታም ልማድ ስንቅ ገ
ንዘብ ለሌላቸው ስንቅና ገንዘብ እየሰጠ
ች እንግዶችን እበር ድረስ መሸኘት ል
ማዷ ስለሆነ ያም ሥዕሏን ደብቆ የያዘ
ው መነኩሴ እወጣለሁ እያለ ሲያስብና
ሲሞክር ሳይቻለው ባየችው ጊዜ አንተ
አባቴ ሆይ በታመመ ሰው አምሳል እይ
ሃለሁ እወጣለሁ እያልህ ከበር ትደርሳ
ለህ አይሆንልህም ፡ እደር ነገ ጧት
ትሄዳለህ አለችውና አደረ ፪ተኛ እሄ
ዳለሁ ብሎ ተነሣና ቢሞክረው እን
ደ ትላንቱ መሔድ ተሣነው እሷም
እደር ብላ ሁለተኛ ቀን አሣደረችው በ
፫ተኛው ቀንም እንደዜሁ እሔዳለሁ
ብሎ ተነሣና በሩን መውጣት ተሣነው አ
ልቻለም ማርታም ፫ ቀን ሙሉ እንደዚ
ህ ሆኖ እንደ በሽተኛ ሳይተኛ ስላደረ ጤ
ና አይደለህም ተናገር ፣ የሠራኸው ሥራ
አለ? አለችው ያም መነኩሴ ገመናው
ስለተገለጠ በማፈር ነገር ጀመረ እቴ
ሆይ አሁን ባለፈው ወር ወደ ኢየሩሳሌ
ም በሔድሁ ጊዜ የእመቤታችንን ሥዕ
ል አምጣልኝ ያልሽኝ እኔ ነኝ አላወቅ
ሽኝምን አላት እሷም ከቤቴ የሚወጡና
የሚገቡ ብዙ ናቸው በምን አውቅሃለሁ
አለችው ።
ከዚህ በኋላ ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ
እንደሚባለው ሥዕሊን ከገዛት ጀምሮ
የተደረገውን ተአምር ሁሉ ገልጦ ነገራ
ት ይህንም ተናግሮ ያችን ሥዕል ከክን
ዱ አውጥቶ እነሆ ብሎ ለማርታ ሰጣት

ማርታም ይህን ነገር ሰምታ ከእግሩ በ
ታች ወድቃ ስለ እመቤታችን ፍቅር ሰ
ገደች ያችንም ሥዕል ከእጁ ተቀብላ ፡
እሴኒ ንግሥት የጌታችን መስቀል በተ
ገኘ ጊዜ እልል እንዳለችና እንዳመሰገ
ነች ፣ እንደ ሰገደችም ፣ ማርታም ሰገደ
ች አመሰገነች እልልታ አደረገች ።
ያን ጊዜ የሩቁና የቅርቡ ሰው ደስታውን
ሰምቶ እስኪሰበሰብ ድረስ የዳዊት ልጅ
ሰሎሞን ለታቦተ ጽዮን ማደሪያ ቤተ
መቅደስ እንደ ሠራ እሷም ያማረ የሥዕ
ል ቤት አሠራችላት ። ማርታም የተቻ
ላትን ያህል በሌሊትም በመዓልትም በ
ቀኝና በግራዋ ዕለት ዕለት መብራት
ታበራላት ነበር ። በፊቷም እየሰገደች
እጅ ትነሣላት ነበር ሌሊትም አብራ ካ
ጠገቧ ታድር ነበር ። አትለያትም ነበር
ይላል ፣ ታምሯ ይልቁንም የሚያስደን
ቀው ታምራቷ ሰብእ ሰገል ጌታ በቤተ
ልሔም በተወለደ ጊዜ ከልጅዋ ከወዳጅዋ
ጋር አግኝተው እንዳዩዋት ፣ ይችም ሥ
ዕል ሥጋን የለበሰች ትመስል ነበር ።
ከእሷም ወዝ ሲወጣ ይታይ ነበር ። ከወ
ዟም የተቀቡ ሁሉ ከሚያስጨንቅ ደዌ
ያቸውና ሕመማቸው ይፈወሱ ነበር ይላ
ል ። ይህች የከብርት እመቤታችን ሥ
ዕል ከኢየሩሳሌም የማርታ አገር የመሪ
ና ቦታ ወደምትሆን ጴጄንያ ወደምት
ባል አገር ፣ በመስከረም ፲ ቀን እንደ ደረ
ሰች በዓለም ዳርቻ ሁሉ ተሰማ ፡ ይህች
ንም ቀን ያከብሯት ዘንድ ሊቃነ ጳጳሳት
ወስነዋል ።
አሁንም በረከቷ ረድኤቷ ልመናዋ
ክብሯ የልጅዋ የወዳጅዋም ቸርነት በ
ውነት ለዘላለም አድሮብን ይኑር አሜን
አባ ቸርነት ጋሻው በዛ



# መስቀል ኃይላችን ነው

ስለመስቀል በምናስብበት ጊዜ በዓ
ይነ ኅሊና መቃኘት የሚገባን የዕፀ መ
ስቀሉን ቅርጽ ሳይሆን በርሱ ላይ ለቤዛ
ዓለም የተሰቀለውን መድኃኔ ዓለም ክ
ርስቶስ ያስገኘውን ታላቅ የመንፈስ
ድል ነው ። አዎ በቀራንዮ /ጐልጐታ/
ላይ የተተከለው መስቀለ ክርስቶስ የዓ
ለም ሁሉ አሳች የሆነው የሰይጣን ዲያ
ብሎስ ራስ ተቀጥቅጦ የወደቀበት የመ
ንፈስ ድል ዓርማ ነው ።
መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ በዚያ መስ
ቀል ላይ በማያዳግም ሁኔታ ለአንድ
ጊዜ ያን ሁሉ መከራና ሞት ድል ነሥቶ
በአሸናፊነት መውጣቱ በእምነት ለምን
ከተለው ሁሉ ታላቅ መመኪያ ክብራች
ን መሆኑን አስመስክሮአል ።
በሥጋ ከይሲ ተሰውሮ የመጀመር
ያዎቹን ሰዎች በአሳተበት በሰይጣ
ን ዲያብሎስ ላይ የዕርግማን ፍርድ
ባስተላለፈ ጊዜ ‘‘በአንተና አንተ ባሳት
ሃት ሔዋን መካከል ጠላትነትን እመሠ
ርታለሁ፣በዘርህና በዘሯም መካከል ጠ
ላትነት እንዲኖር አደርጋለሁ ፤ ከዚህ
ም የተነሣ አንተ የሔዋንን ልጆች ስኰና
ትነከሳለህ ከሄዋን ዘር የሚወለደውን
መድኀኔዓለም ክርስቶስም የአንተን ራ
ስ በመስቀሉ ይቀጠቅጣል’’ሲል እግዚ
አብሔር እምላክ የሰጠው ኪዳን አዳም
የተፈጸመውም በዚሁ መስቀል አማካ
ይነት ነው ።
ይህ ነገረ መስቀል የክርስቶስ ተከታ
ዮች የሆኑ ሁሉ የዚህን ዓለም መከራና
ሥቃይ ከምንም ባለመቁጠር ፍጹም የ
ሆነ የሃይማኖት ጥብአት (ጽንአት) እን
ዲኖራቸውና የመንፈስ ጥንካሬ አግኝተ
ው ለዘላለማዊ ድል እንዲበቁ ሞትንም
እንዲንቁ ፣ ሕይወትም አንድ ብቻ አለ
መሆንዋን አውቀው ከዳግም ሞት እን
ዲጠነቀቁ የሚያስተምር የሰማዕትነት
መማሪያ ስሌዳቸው ነው ። ይንንም የመ
ጀመሪያውን ሰማዕትነት ከተካኑት ሊ
ቀ ዲያቆናት እስጢፋኖስ ከሊቀ ሐዋ
ርያት ጴጥሮስ ከታላቁ ምሁር ጳውሎስ
ና ከሌሎችም ታሪክ መማር ይቻላል ።
ማንኛውም የሀገር ዜጋ ሀገሩን ከወ
ራሪ ጠላት ለመከላከል በውድም በግድ
ም የሕይወት መሥዋዕትነት መክፈል እ
ንዳለበት ሁሉ ሰማያዊት አገር ገነት መ
ንግሥተ ሰማያትንም ለመውረስ ይህኑ
ዓይነት ተጋድሎ ይጠይቃል ። ጽንዑ
እስመ እነ ምእከዎ ለዓለም እኡ ዓለምን
እንዳሸነፍሁ እናንተም እንዲሁ በአሸ
ናፊነት ለመውጣት ጽኑ’’ ሲል መድኅ
ኔ ዓለም ክርስቶስ በወንጌል ያስተማረ
ውም ይህንኑ ነው ።
ከዚህም በቀር እኔን መከተል የሚወ
ድ መስቀሌን ይሸከም ’’ የሚል ትዕዛዝ
መስጠቱ ተጽፎአል /ማቴ ፲፮.፳፬/ ።ቀ
ጠል በማድረግም ሲናገር ነፍሱን ለማዳን
የሚወድ በማዳን ፈንታ ከነጭርሱ ያጠ
ፍታል ፣ ስለ እኔ ነፍሱን የሚያጠፋ ግን
መልሶ ያገኛታል ። ካለ በኋላ ማንኛውም
አማኝ የሆነ ሁሉ ሆዴ ይሙላ ደረቴ ይ
ቅላ በማለት’’ዓለምን ቢገዛ ቢነዳ ምን
ይረባል ? ምንስ ይጠቅመዋል ? ወይስ
ሰው ስለነፍሱ ቤዛ ምን ዋጋ ሊከፍልላ
ት ይችላል ?። ሲል ይጠይቃል ።
ስለዚህ መስቀል ኃይላችን ነው ስንል
ቅርጹን የመሸከም ምልክት ብቻ ሳይ
ሆን የመሥዋዕትነት ዓርማ የድል ዓር
ማ መሆኑን ማጤን ይገባል ። በዕርግጥ
ቅርሳዊ ምልክትነቱም ይሠራል ። እን
ደሥዕላዊ ማስረጃ ሆኖ ይታያልና ነው።
ለምሳሌ የ3ኛው ምዕት ዓመት መደ
ምደሚያ መሪ የነበረው የሮማ ንጉሠ
ነገሥት ቆስጠንጢኖስ የክርስትና ሃይ
ማኖት ተከላካይ ጠበቃ ሆኖ በተነሣበ
ት ወቅት ‘‘በዝ ትእምርተ መስቀል ት
መውእ ፀረከ በዚህ የመስቀል ምልክት
ነት ጠላትህን ድል ትነሣለህ’’ የሚል
ቃል በጸፍጸፈ ሰማይ ላይ ተጽፎ በ
ራእይ ስለ ታየው ወዲያውኑ በየጦሩ
መሣሪያና የመለዮ ልብስ በየፈረሱ
ም ልጓም ላይ የመስቀል ቅርጽአሠርቶ
በመገለሙ የማያዳግም ድልን ተቀዳ
ጅቶ መመለሱ በዓለም ታሪክ ተመዝግቦ
አል ። በሀገራችንም ደግሞ ይኸው ምሳሌ
ነት ብዙ ተካታይ ስላለው በተለይ ክርስ
ቲያኑ ሕዝብ የመስቀልን ቅርጽ ከብር
ና ወርቅ ብቻ ሳይሆን በሰውነቱም ላይ
በንቅሳት መልክ የሚያሠራው ብዙ
ነው ።
ነገር ግን ቅርጽ ብቻውን የመስቀልን
ምንነት አጉልቶ ማሳየት ስለማይችል እም
ነት ተቀዳሚ ሆኖ በጎ ምግባር ሊከተለ
ው ይገባል ። ሐዋርያ ጳውሎስም ወደ
ቆሮንቶስ በላከው ቀዳማዊ መልእክት
ምዕ.፩.፲፰‘‘ የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉ
ት ሞኝነት ነው ለምንድንበት ለእኛ ግን
የእግዚአብሔር ኃይል ነው ይላል የሚ
ያስተምረን ዋና ቁም ነገር ይህኑ እንደ
ብሎን ሚያጠነክር ነው ።



መድኀኒ ዓለም ክርስቶስ ለቤዛ ዓለም
መስቀሉንና መችንከሩን በዚያም መስቀል
ላይ ሣለ ጐኑን በጦር መወጋቱን ተጠማ
ሁ ባለ ጊዜ ወሀቤ ዝናም መሆኑን ዘነግተ
ው የተደባለቀ ኮምጣጣ ሐሞትና ከርቤ
ያጠጡት መሆኑን ከዚያው መስቀል ላይ
ሣለ ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት ሥጋው
በፈቃዱ በለየበት ሰዓት ‘‘ተፈጸመ ኩሉ’’
ሁሉ ነገር እነሆ አሁን ተፈጸመ’’ ሲል መ



www.ethiopianorthodox.org

ናገሩን እንዲሁም "አባት ሆይ የሚያ ደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው በማለት ለጠላቶቹ አይሁድ እንኳ የጸለየ በትና ሕይወቱን የሰጠበት መሠዊያ መሆኑን ዘንግተው በቅርጽ ምልክትነት ብቻ እንጠቀምበታለን የሚሉ ቢኖሩ ግን የስም ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው ።

ስለዚህ የክርስቶስ መስቀል ከንቱ እንዳይሆን የምሥጢሩን ምንነት ተር ጉመን ልንረዳ ይገባናል ። መስቀል ኃይ ላችን ፣መስቀል መመኪያ ክብራችን መስቀል የድል አርማችን ሆኖ የሚገ ኘው ይህኑ ስንገነዘብ ብቻ ነው ።

አሁንም በመስቀሉ እግዚአብሔርና ሰውን ያስታረቀ በቤተ አይሁድና ከአረ ማውያን ወገን ባመኑት መካከል የነበረ ውን የጥል ግድግዳ ያፈረሰ ፣ በመስቀሉ ዘላለማዊ የመንፈስ ድልን በማቀዳጀት ፍቅርና ሰላምን ያነገሠ፣በሞቱኃይል ሞትን የደመሰሰ በመንፈስ ቅዱስ ልጅነት ሕይ ወትን ያደሰ በኃጢአት አሜከላ የቆሰለ ውን የአማኞች ሕይወት በደሙ ፈሳሽ ነው የፈወሰ መድኀኒ ዓለም ክርስቶስ ለዘለዓለም ቅዱስ ስሙ የተመሰገነ ይሁ ን ። አሜን ።

ቄስ መክብብ አጥናው

# አንጢላርዩስ

ከገጽ ፳፭ የዞረ

እንዲያውም ከዓመት ጉርስና ከዓ መት ልብስ የበለጠው ሀብትና ንብረት አከብተው እንደገና ለብዙ ዓመታት በማሰብ ለችግረኛ ከመሥጠት ቢከለ ክሉና እህሉንም ሆነ ልብሱን ብልና ነቀዝ ቢበላው ምቀኝነት ከመሆኑም አልፎ በቃሉ ሀሰት የሌለበት እግዚአ ብሔርን ከዳተኛ ማድረግ ነው ። በተ ለይም በዝናብ አብቅሎ በፀሐይ አብ ስሎ የሚመግበውን አምላክ መጠራ ጠርና ርሕራኄውን ማስተሐቀር ይሆ ናል ።

ለዚህም በማቴዎስ ወንጌል ፯ ፡ ፳ "ሀልፈትና ጥፋት የሌለበት ሰማያዊ ድልብን አድልቡ " ሲል ለድሆች የምንሠጠው ምጽዋት ሁሉ በማይጠ ፋው በእግዚአብሔር ፊት የሚከማችና ጸጋና ክብር የሚሰጠን መሆኑን ያስተ ምረናል ።

እንግዲህ በመልኩና በምሳሌው ፈጥ ሮ ያከበረው የሰው ልጅ በችግር ወጥ መድ ውስጥ ገብቶ ሲጨነቅና ሲሰቃይ እያዩ አለማዘንና ርሕራኄ አለማድ ረግ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ክልል ውጭ መውጣት መሆኑን ልንረዳ ይገባል ። ይህን ተረድተው መሥራት ሲችሉ አንድ ጊዜ አምነው ከተጠመቁ በኋላ መልካም ሥራ መሥራት አያስፈልግም በማለት ለችግረኞች መርዳት ሲችሉ ባይሠጡና ባይራሩ እግዚአብሔር አይራ ራላቸውም ይላል ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ። ፪ ጴጥ ፪ . ፬ ።

ስለሆነም በአረማመዳችንና በሥራ ችን ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ ብናሠ ኘው በሰው ልብ ያልታሰበችና የሰው ነይን ያላያትን አዲስምድርንና አዲስ ሰማ ይን ያለጥርጥር ያወርሰናል ፪ኛ ጴጥ ፫ ፡ ፲፫ ። በማለት ያስተማረንን ቅዱስ ቃል በሥራ ልንተረጉመው ይገባናል ርሕ ራሄውና ቸርነቱ በእኛ አድሮ ከእግዚአ ብሔር በተሠጠን ጸጋና ብዕል በጐ ሥራ ሠርተን መልካም ፍሬን ለማፍራት እን ችል ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን ።

አባ ብርሃነ መስቀል አየሁ



# በጸበሉ ፈዋሽነት የታወቀው ማቢ አቦ መካነ ሕይወት ገ/ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ ተደበረ

ማቢ አቦ የሚገኘው በጐንደር ሀ/ስ ብከት በደብረ ታቦር አውራጃ በእስቴ ወረዳ ነው ። ይኸው ደብር ከብፁዕ ወ ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮ ጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያ ን ፓትርያርክ በተፈቀደው መሠረት የ ካቲት ፲፰ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. መካነ ሕ ይወት ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ መ ሠየሙን ዘግይቶ የደረሰን ዜና አስረ ድቷል ።

በተሠየመበትም ዕለት በዓሉ ሲከበ ር እንዲመጡ ጥሪ የተደረገላቸው አድ ባራትና ገዳማት ፭፻፭ ናቸው በዚሁ በ ዓል ላይ

የእሴቴ ወረዳ ሊቀ ካህናት መለሰ ኃይሉ የወረዳው ቤተ ክህነት የሰበካ ጉ ባኤ አደራጅ አቶ አያሌው ካሣ ከአዲስ አበባ መምሪያ ትእዛዙ ከበደ ተገኝተ ዋል ።



ታቦቱ ወጥቶ ዑደት ሲደረግ

ከበዓሉም ላይ ከተገኙት ካህናት በ ከፊል

፩/ የመካነ ኢየሱስ ካህናት

፪/ የጋፋት ተክለ ሃይማኖት "

፫/ የየቁራ ጊዮርጊስ

፬/ የየቁራ ማርያም

፭/ የየቁራ ኢየሱስ

፮/ የአጋጥ ጽዮን

፯/ የዳጉት ኢየሱስ

፰/ የዘንጃ መርምህናም

፱/ የወቃጭት መድኃኔ ዓለም

፲/ የሙሳፋ ማርያም

፲፩/ የሽማግሌ ጊዮርጊስ

፲፪/ የዙገራ ገብርኤል

፲፫/ የአጭቃን ኪዳነ ምህረት ካህናት ወዘተ ተገኝተዋል ።

እንዲሁም በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ም እመናን የበዓሉ ተካፋዮች ሆነዋል ። ከዋዜማው ጀምሮ እስከ በዓሉ ፍጻሜ ድረስ ካህናቱ ከቤተ ክርስቲያኑ በመገ ኘት ስብሐተ እግዚአብሔር አድርሰዋ ል ።

በበዓሉ ዕለት ታቦቱ ከመንበረ ክብ ሩ ወጥቶ ቤተ ክርስቲያኑን ሦስት ጊዜ ያት ዞሮ በአውደ ምህረቱ ላይ እንደ ቆመ የሰበካ ጉባኤው አደራጅ አቶ አያ ሌው ካሣ ገለጻ አድርገዋል ፣ ባደረጉት ም ገለጻ ደብሩ የተተከለው በዓፄ ይኩኖ አምላክ ሲሆን የተከሉትም ተክለ ጊዮ ርጊስ ናቸው ከመቅደሱ ደጃፍ ከላይ ወደታች ፀበል ይፈልቃል በጸበሉም እ የተጠመቁ ብዙ ሕሙማን ተፈውሰዋል በመፈወስም ላይ ናቸው ካሉ በኋላ ቤተ ክርስቲያኑ የማር ክዳን በነበረበት ጊዜ ሁለት አሞሮች የጉልላቱን ማር እየመ ዘዙ መጣል ሲጀምሩ ማሩን እንደነከሱ ሞተው ካህናቱና ምእመናኑ ባሉበት ተንከባለው ወድቀዋል ። ብለዋል ።

አቶ አያሌው ማብራሪያቸውን በመ ቀጠል በቆየው ባሕል መሠረት ሕዝቡ ከቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ተሰብስበው አፍርሳታ ለማውጣት ሲንጫጩ ም ንም ደመና ሳይኖር ከጠራው ሰማይ መ ብረቅ ወርዶ ከሕዝቡ አጠገብ የነበረው ን ጥድ ከሁለት ጐረደው ሕዝቡም ፈር ተው ትበተኑ ለሁለተኛ ጊዜ በአፍርሳ ታ ምክንያት ከቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ መሰብሰባቸውን እርግፍ አድርገው ት ተዋል ።

በመብረቅ ኃይል የተጐረደው ጥድ ግን ተተክሎ እንደገና ሲያለመልም ከ ጉራጁ ላይ ፀበል ፈልቋል ጸበሉም ሕ ሙማንን በመፈወስ ላይ ይገኛል ፣ ጣሊ ያንም ሀገራችን ኢትዮጵያን በወረረበ ት ዘመን ጠላት ቤተ ክርስቲያኑን ለማ ቃጠል በአይሮፕላን ቢደበድበው አል ቃጠልም ስላለው እንደገና በእግሩ መ ጥቶ ለማቃጠል ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ሊገባ ሲል የአንግሊላ ስለወደቀ ደንግጦ ሳያቃጥለው ተመልሶ ሂዷል።

በእብድ ውሻ የተለከፈ ሰውም ወደ ዚህ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ሥጋውንና ደሙን ተቀብሎ ጸበሉን ወጥቶ ከሔደ ጉዳት ሊደርስበት አይችልም ።

በዚህ ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙት ተአምራት በአጭር ጊዜ ተነግረው የ ሚፈጸሙ አይደሉም ለማስረጃ ያህል ግ ን ጥቂቶቹን ጠቅሰናል በማለት አቶ



www.ethiopianorthodox.org

ካያሌው ካሣ ንግግራቸውን እንደፈጸሙ መምሬ ትእዛዙ ከበደ ምዕራገ ጸሎት አድርገው ሥርሆተ ሕዝብ መሆኑን ዜናው ገልጿል ።

በበዓሉ ላይ የተገኙት ካህናትና ምእመናን ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ለብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ የሀ/ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ረዥም ዕድሜና ጤና በመመኘት የተሰማቸውን መንፈሳዊ ደስታ በጭብጨባ መግለጻቸውን በተጨማሪ ዜናው አስረድቷል ።

ይህንን የመሰለ መንፈሳዊ ክብር ለመጐናጸፍ የሚመኙ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት መኖራቸውን አስታውሶ ለቅዱስ ፓትርያርኩ ዘለግ ያለ ዕድሜ በመመኘት ዜናው እሳቡን አጠቃሏል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አሁን በሁሉም አቅጣጫ በማደግ ላይ ስለምትገኝ ይህ መንፈሳዊ ዕድገቷ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንዲሄድ ለቅዱስነታቸው ጤናማ ዕድሜ እንዲሰጥላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አዘውትራ ትጸልያለች ።

የዜናው አቅራቢ
መምሬ ትእዛዙ ከበደ

## ቅድስት አርሴማ

ከገጽ ፳፩ የዞረ

ሙሽራ ነሽ እንጂ የዚህ የከሃዲ አይደለሽም አለቻት ።

አርሴማም ከዚህ የሚከተለውን የዳዊት መዝሙር፡ጸለየች ‘‘አቤቱ በጆሮአችን ሰማን አባቶቻችንንም በዘመናቸው የሠራነውን ሥራ ነገሩን እጅህ አሕዛብን አጠፉች እነርሱንም ተከልህ አህዛብንም አሰቀየሃቸው አሳደድካቸውም በሰይፋቸው ምድርን አልወረሱም ክንዳቸውም አላዳናቸውም ቀኝህና ክንድህ የፊትህም ብርሃን ነው እንጂ ወደሃቸዋልና አምላኬና ንጉሤ አንተ ነህ ለያዕቆብ መድኃኒትን አዘዝክ በአንተ ጠላቶቻችንን እንዋጋቸዋለን በስምህም በላያችን የቆሙትን እናዋርዳቸዋለን በቀስቴ የምታመን አይደለሁምና ሰይፌም አያድነኝምና አንተ ግን ከጠላቶቻችን አዳንኸን የሚጠሉንንም አሣፈርሃቸው ሁልጊዜ በእግዚአብሔር እንከብራለን ስምህንም ለዘለዓለም እናመሰግናለን አሁንም ነፍሴን ተቀበላት እያለች የመጨረሻ ልመናዋን አቀረበች መዝ. ፵፫ ቁ. ፩-፰

ንጉሡም በእነጋገሯ በድፍረቷ እየተደነቀ በውበቷም እየተገረመ ተይ ምን ያደርግልሻል ? ሃሣብሽን ለውጭው እኔ በወርቅ በአልማዝ አስጌጥሻለሁ ንግሥትም አደርግሻለሁ ሲል አባበላት።

እርሷ ግን መንፈሰ ጠንካራ ስለነበረች ለእኔ ግን ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ብል የማይበላው የክብር ልብስ ፥ በገንዘብ የማይለካ የዘለዓለም ክብር እንደሚሰጠኝ ስለማምን ገንዘብህ ለጥፋትህ ይሁንህ ስትል መለሰችለት ።

እርሱም በድፍረቷ ስለተናደደ በሰይፍ እንዲገድሏት አዘዘ ። እርሷም የተዘጋጀውን የሞት ፅዋ ተቀብላ በክብር አረፈች

በእርሷ ንዴት የተነሣ ጓደኞቿንም አስፈጇቸው በዚህ አኳኋን እርሷም ሆነች ጓደኞቿ የሰማዕትነት አክሊልን ተቀዳጁ ከዚህም የተነሣ ስለሕይወት ታሪኳ የተጻፈው መጽሐፍ እንደሚለውም የቤተ ክርስቲያናችንም ታሪክ እንደሚያብራራው በእርሷ ይህን ግፍ የፈጸመው ድርጣድስ የተባለው የአርማንያ ንጉሥ እርሷ ከሞተች በኋላ በሰላም አልኖረም ሌላ ቀርቶ በሕልሙ እርሷን እየመሰለ ምትሃት ስለሚታየው የመንፈስ ጭንቀት አደረበት ይኸውም ሰይጣን በፊት ክፉ ማሠራት በኋላ ማሰዐት ልማዱ ነውና

ይህ እንዲህ እያለ ለጥቂት ዓመታት ያህል እንደናቡከደነጾር አውሬ ሆኖ በበረሃ ይኖር ጀመር ይባላል ለዚህም ንጉሥ አንዲት ደግ እህት ነበረችውና ስለወንድሟ ስትጨነቅ አንድ ቀን አንዲት መበለት ከመታመሙ አስቀድሞ በግዞቱ ላይ ሳለ ጐርጐርዮስ የተባለውን መነኩሴ ስለ ክርስትና ሲያስተምር ሰምቶ አሥሮት የሚኖር አለ ለእርሱም እህል ውሃ እየወሰድኩ የማቀብለው እኔ ነኝ አሁንም ይህ ሰው ቅዱስ ነውና ከታሰረበት አስወጥተሽ ብትለምኚው ያድንልሻል አለቻት እርሷም ጐርጐርዮስን ከታሠረበት አስወጥታ እንዲያድንላት ለመነችው እርሱም ፈቃደኛ ሆነና እስከ አለበት በረሃ ድረስ ሄዶ ካገኘው በኋላ ጸልዮ ከበሽታው አዳነው ንጉሡም ስለሠራው በደልና ስለፈጸመው የግፍ ሥራ ተፀፅቶ ንስሐ ገባ በመጨረሻም ወደ ዙፋኑ በተመለሰ ጊዜ ጎርጎርዮስን የአርማንያ ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ የሾመው እርሱ መሆኑን ታሪክ ይገልጻል ።

የጻድቅ ሞቱ እረፍቱም ሕይወቱም ነው እንደሚባለው ሁሉ የቅ/ አርሴማም መሞት ለእርሷ ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ ስም ታስረው ለነበሩት ክርስቲያኖች ሁሉ ሕይወት ሆናቸው ከእሥራታቸውም ተፈትተው እረፍት እንዲያገኙ ረዳቸው ቅ/ ጳውሎስም እንዲህ ያለው መከራ በክርስቲያኖች ላይ በየጊዜው እንደሚፈጸም ስለአወቀ በ፪ኛ ጢሞ. ም. ፬ቁ፭-፱ ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ ጽፎለታል ‘‘ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ መከራን ተቀበል የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ አገልግሎትህን ፈጽም በመሥዋዕት እንደሚደረግ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና የምሄድበትም ጊዜ ደርሷል መልካሙን ገድል ተጋድልኩ ሩጫዬን ጨርሻለሁ ሃይማኖቴንም ጠብቄአለሁ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል እያለ ይተነትናል ቅ/ ጳውሎስ የመጨረሻ ትምህርቱን አስተላልፎ ሃይማኖታዊ ግዴታውንም ፈጽሞ እንዳለፈ ሁሉ ቅ/ አርሴማም ከመጻሕፍት ባገኘችው ትምህርት መሠረት መልካም ገድልን ተጋደለች ሃይማኖቷን ጠበቀች ሩጫዋን ጨረሰች የአላዊ ንጉሥ እጮኛ ከመሆን ይልቅ የክርስቶስ እጮኛ መሆንን መረጠች የክብር አክሊልንም ለመቀዳጀት በቃች ይህንንም የመሰለ ገድል በመጋደሊ ከመልካም ሽቱ መልካም ስም ይሻላል እንደተባለው ሁሉ መልካም ስምን አተረፈች ።



# የዋልድባ ገዳም ታሪክ

ዋልድባ የሚባለው ታላቁ ገዳም በኢትዮጵያ ሰሜን ጐንደር ክፍለ ሀገር በሰሜን አውራጃ ውስጥ በተከዜ ዳር የሚገኝ ታሪካዊ ገዳም ነው ።

ገዳሙ የተመሠረተበት ቦታ ለጥ ያለ ሜዳ ሁኖ በደን የተሸፈነ ነው የአየሩ ጠባይ ፍጹም የሆነ ቆላ ስለሆነ ዓየር የሌለው የወባ በሽታ የሰለጠነበት የተዋህስያን መፈጠሪያ ነው ። የደኑ ዓይነት ወይራና ጥድ ሾላና ዋርካ ዋንዛና ብሳና እንብሳና ታሎ አጋምና ቀጋ ግራርና አጣጥ ክርክራና ዲማ ወይባና አባሎ ቁልቋልና ኮሽም ሲሆኑ የምግብ ዓይነቶች ደግሞ ቋርፍና መገ ሎሚና ጋጋዬ ናቸው ። እነዚህን ደኖችና እትክልቶች የሚያጠጡ ወንዞች አባ ኖፀ ዮርዳኖስ ማይበራዝዮ ማይሎሚ ማይለበጣ የሚባሉ ወንዞች ናቸው ። ንብና ጣዝማ በብዛት ይገኛል ። የዱር አራዊት በየዓይነቱ በብዛት ይገኛሉ ። ከዋሻዎች ደግሞ ማይ ለበጣ በዓተ ንጉሥ በዓተ ንግሥት መቃብረ ሳሙኤል እየተባሉ የሚጠሩ ዋሻዎች ሲገኙ ለጥ ካለው ሜዳ መካከል ዋልድባ ላይ ስውር ቁስቋም የሚባል ከፍተኛ ዓንባ ይገኛል ። ገዳማውያኑ መነኮሳት የሚመገቡት ቋርፍ ጣብሬ የሚባል እንደ ድንች ከመሬት ተቆፍሮ የሚወጣ የነጩ ሽንኩርት ዕራስና ድንች መሳይ ነገር ነው ይህ ቋርፍ እንደ እሬት የሚመርና ምላስ የሚጐለጉል ኃይለኛ ነገር ስለሆነ ከመሬት ተቆፍሮ ከወጣ በኋላ ተቀቅሎ ሲበስል ተመልጦና ተከትፎ ይሰጣል ሲደርቅ በቅርጫት አድርጐ ከፏፏቴ ውሃ ላይ ከሰባት ቀናት በላይ ይሰነብታል ። ከዚያም ወጥቶ ይሰጣና ሲደርቅ ከደረቀ ጥሬ ሙገ ጋር በቅርጫት ይቀመጥና ለመነኮሳቱ በተግባር ቤቱ ኃላፊ ይቆነናሉ መነኮሳቱም ያን ተቀብለው እንደገና ቀቅለው ይመገባሉ ።

ስሊጥና ኑግ ከማር ጋር መበያ እንዲሆናቸው በሩጋ መሳይ ይታደላሉ።ይኸውም የሚሆነው በደወል ድምፅ ነው የዋልድባ ገዳም የመሬቱ ስፋት 3 ቀን ያስጉዛል። የዋልድባ ገዳም አዋሳኝ ወንዞች ተከዜ እንሲያና ዘሬማ ናቸው ገዳም ማለት ጭው ያለ በረሐና ጫካ የበዛበት የሰው ድምፅና የዶሮ ጩኸት የማይሰማበት የዱር አራዊት የሚኖሩበት ከዓለማውያን ሰዎች ገለልተኛ የሆነ ማለት ነው ከኢትዮጵያ ገዳማትም ቀደምትነት ያለው ይህ ዋልድባ የሚባለው ገዳም ነው ይኸውም ገዳም ጤፍና ጥሬጥሬ ሥጋና ወተት ጠላ የማይቀመስበት የሞቀና የደመቀ ጌጥ ያለው ልብስ የማይለበስበት የሴት መናኝ መነኮሳት የማይቀመጡበት ፍጹም የሆነ ታላቅ ገዳም ነው ። በዋልድባ ገዳም ውስጥ የሚገኙት ታቦታት ከሶስት ቦታ ላይ ሁኖ ስማቸውም አብረንታንት መድኃኔ ዓለም ሰቋር ኪዳነ ምሕረት ዳልሻን ኪዳነ ምሕረት እየተባሉ የሚጠሩ ናቸው ።

በዚህ ገዳም የሚገኙ መነኮሳትና መናንያን በአንድነት ሠርተው በአንድ ዓይነት ምግብ በአንድ ዓይነት ልብስ ተወስነው ይኖራሉ እንጅ ከፍና ዝቅ ያለ አስተዳደር የለባቸውም የነዚህም መነኮሳት አስተዳዳሪ ድንግል መነኩሴ የሆነ ቀሞስ አንድ መምህር በገዳማውያኑ ተመርጦ ያስተዳድራል ። በውስጡ ግን እንደራሴ እያደረገ የመሾም ሥልጣን አለው ።

በዋልድባ ገዳም የውሃ ችግር የለም የዱር አራዊትም መነኮሳቱን አይተናኳኰሉም መነኩሴውና አንበሳው በአንድ ላይ ይውላሉ ። በገዳሙ ውስጥ ላምና በሬ በግና ፍየል በማለት የቀንድ ከብትና የጋማ ከብት በፍጹም የለም እትክልቱም የሚተከለው በእጅ በዶማ ቆፍሮ ብቻ ነው በዋልድባ የማገዶ ችግር የለም የዚህ ታሪካዊ ገዳም አመሠራረቱም እንደዚህ ነው በሸዋ ክፍለ ሀገር በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ቡልጋ ውስጥ ልዩ ስሙ በረከት መንደር አብየ ገዳም መድኃኔ ዓለም ከሚባል ቤተ ክርስቲያን በ484 ዓ.ም. ጥር 11 ቀን በዓለ ጥምቀትን ለማክበር ታቦት ከወንዝ እ ወርደው ድንኳን ጥለው ካህናቱ በውዝዋዜ ሕዝቡ በጨፈራና በዘፈን ሲለዋወጡና የማይገባ ሥራ በመሥራት የቅዳሴውን የመግቢያ ሰዓት በማሳለፋቸው እንደ የበቃ ባሕታዊ በትዕዛዘ እግዚአብሔር ድንገት መጥቶ ቅዳሴውን በወቅቱ ግዑዛን ቅዱሳን ቀድሰውታል በእናንተ ግን ከፍተኛ የሆነ መዓት ታዝዞባችኋል የነፍሳችሁን ደኅንነት ፈልጉ አላቸው እነሱም አባታችን ሆይ ምን ብናደርግ እንማራለን አሉት እርሱም ኢየሩሳሌም ሄዳችሁ በቀራንዮ ላይ ብታለቅሱ እግዚአብሔር ይቅር ይላችኋል አላቸው እነርሱም ወደቤታቸው ሳይመለሱ ታቦታቸውን ታቦተ መድኃኔ ዓለምን እንደያዙ ሳይጠራጠሩ በእምነት ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ጉዞአቸውን ቀጥለው ሲሄዱ የነሱን መሄድ የሰሙ ባጠገባቸው ያሉት ሕዝቦች ተከተሉአቸው የተከተሉአቸውም መናኞች እስኪደርሱ ድረስ ሣይንት ላይ ሰፍረው ቆዩአቸው ።

ከዚያ በኋላ የፊተኞቹና የኋለኞቹ በአንድ ላይ ሁነው ጉዞ ሲጀምሩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃናዊ ጐልማሳ መስሎ ቢታያቸው ምን ያምር አማሪ ነው አሉ በዚህ ምክንያት አገሩን አማራ ሣይንት አሉት ከጊዜ ብዛት በኋላ አማራ ሳይንት ተብሏል ይባላል በዚያም የተገለጸላቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወዴት ትሄዳላችሁ ብሎ ጠየቃቸው ኢየሩሳሌም እንሄዳለን አሉት መልካም ነው ። እኔ እምራችኋለሁ ብሎ መንገዳቸውን በቀጥታ ወደ ሰሜን የነበረውን ትቶ ወደ ሰሜን ምዕራብ እየመራ ጐንደርን አድርጐ ሰቋር አደረሳቸው ።

ከሳይንት ተነሥተው ሰቋር እስኪደ



www.ethiopianorthodox.org

ርሱ በነሱ ንግግር ስም የወጣላቸው ብዙ ሀገሮች አሉ ከዋልድባው ደንበር ሰቋር በደረሱ ጊዜ ፈጣሪያችሁን ከዚህ ብታገኙት ወደ ኢየሩሳሌም ከመሄድ አትቀሩምን አላቸው እነሱም ፈጣሪያችንን ካገኘን ሌላ ምን እንፈልጋለን አሉት እርሱም ፈጣሪያችሁ እኔ ነኝ አላቸው እነሱም እኛ መንገድ እየመራኸን ብትመጣ ደግ ሰው መስለህን ነበር ለካስ እንደዚህ ያለህ መስሕቱ ሰይጣን ነህ አሉት።

እርሱም እንግዲያስ ምን ባደርግላችሁ አምላክ መሆኔን ታምናላችሁ አላቸው ይህችን በፊታችን የምናያትን ገደል ነድለህ ብታሳየን እናምናለን አሉት ወዲያውኑ በያዘው ዘንግ ወርውሮ ዓንባዩቱን ሲነድላት አይተው ገደሉን ሽንቁር እንጅ ቀደደው ነደለው አሉ ስለዚህ ይህ ገደሉ የተነደለበት ቦታ ሰቋር ተብሎአል ። እስከአሁንም ቀዳዳዋ ትገኛለች እነሱም ጉዳዩ አስደናቂ ቢሆንም ምትሐት የሰይጣን ተንኮል ሊሆን ይችላል ሌላ ከዚህ የበለጠ ካላየን አናምንም ብለው ጉዞአቸውን ቀጥለው ሲሄዱ ጌታም እንደተለመደው እየመራቸው በዓጼ ላሜዳ ዘመነ መንግሥት መጋቢት ፳፯ ቀን አብረንታንት ደረሱ ጌታም በሉ ዳግመኛ ምን ምልክት ባሳየኋችሁ ታምናላችሁ አላቸው እነሱም እውነት የባሕርይ አምላክ ከሆንህ ከሀገራችን ከወጣን ጀምሮ ከዚህ እስከንደርስ በሞት በሕመምና በድካም የተለዩትን ወንድሞቻችንን በአንድ ላይ ሰብስበህ ብታሳየን እናምናለን አሉት የሞቱትን አስነሥቶ የደከሙትን አበርትቶ የታመሙትን ፈውሶ በአንድ ጊዜ ሰብስቦ በአብረንታንት ላይ አገናኛቸው እነሱም አምላክ መሆኑን አመኑበት ሰገዱለትም ይህን ካሳየቸው በኋላ ጌታ ይህ ቦታ ኢየሩሳሌም ይሁንላችሁ በዚህ ቦታ የተቀበረ አይወቀስ አይከሰስ ኃጢአት አይሻገርበት እህል አይበላበት ብሎ ቦታውን ባረከላቸው እነሱም ይህ ቦታ ኢየሩሳሌም ይሁንላችሁ ካልከን ጉባኤ አይሁድን ሠርተህ በዕለተ ዓርብ በኢየሩሳሌም ላይ የተቀበልከውን መከራ ሁሉ አሳየን አሉት ጌታም ከነሱ አንዱ መናኝ አንዲትየወይራ መቆጠሪያ ፍሬ ነሥቶ ተክሎ ወዲያውኑ በአንድ ሰዓት ውስጥ አብቅሎ ዛፍ አድርጎ ጉባዔ አይሁድን ሠርቶ በዚችው ዛፍ ላይ ተሰቅሎ በዕለተ ዓርብ የተቀበለውን መከራ ሁሉ ገለጸለት በዚህ ጊዜ ለመስቀልህ መስገድ ይገባናል ። ብለው ሰገዱለት ይህን አደረክልን የተጠመቅህበትን ዮርዳኖስ የት እናገኛለን ቢሉት ከሦስት ቦታ ውሃ አፍልቆ ከዚህ የተጠመቀ ዮርዳኖስ ይሁንለት ብሎ ባርኮ ሰጣቸው ከዚህ በኋላ በዮርዳኖስ ውሃ እያጠመቀ የድንጋይ ቆብ እየቀረጸ ደፋላቸው በግብረ አምላክ ጥሩ ሁኖ በጌጥ የተሠራ ቤተክርስቲያን አስገኝቶ ከሀገራቸው ባመጡት መድኃኒዓለም ታቦት ላይ ቀድሶ ዘጠና ዘጠኙን መነኮሳት አቁርቦ እንግዲህ ይህ ቦታ ለናንተ ይሁናችሁ ከዚህ ተቀመጡ ብሎ ተሰናበታቸውና ምድሪቱን ሁለት አፍ አድርጎ ከፍቶ ሲገባ ታያቸው እነሱም ከአንተ አንለይም አብረንታንት ጋር ነው የምንሄደው ብለው ወንዶቹ በስተቀኝ ሴቶቹ በስተግራ በተነደለው ጉድጓድ አብረው ተከታትለው ገቡ ጌታም የገቡበትን ምድር እንደ ድንኳን አንሥቶ እነዚህን ከላይ የተናገርናቸውን መነኮሳት ወደ ምድር ውስጥ በሙሉ እንዲገቡ አድርጎ ዳግመኛ እስከ እምመጣ ድረስ ሳትሞቱ ሕያዋን ሁናችሁ ኑሩ ብሎ በምድሯ ውስጥ አስቀምጦአቸዋል ። ይባላል ።

በዚህ ጊዜ ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ብለው ፈጣሪያቸውን ስለአመሰገኑ የገቡባት በር ሃሌ ሉያ ተብላለች ወዲያውኑ ዋሊ የምትባል በምድሯ ተክሎ ምግብ ትሁናችሁ ብሎ ሰጣቸው ይህችም ዋሊ በምድረ ዋልድባ ሞልታ በየፊታቸው እያፈራች ምግብ ሁናቸው ትኖራለች 3 ምንጩ አድርጎ ያፈለቀላቸውን ውሃም ሁለቱን ምንጭ ወደታች አፍስሶ ለነሱ ምግብ አድርጎታል አንዱን ወደ ላይ አመንጭቶ በዚሁ ቦታ ከምድር በላይ ለሚኖሩት መነኮሳት ምግብ አድርጎታል አብረን ታንት ነው የምንሄደው

ባሉበት ቦታዋ አብረንታንት ተብላለች በዕሀዋሊ ገዳመዋሊ ተብላለች ከብዙ ጊዜ በኋላ ከዋሊ ዋልድባ ተብላለች ይህ ሁሉ የተፈጸመው አብረንታንት በገቡበት መጋቢት ፳፯ ቀን ስለሆነ በየዓመቱ የስቅለቱና የመስቀሉ በዓል የሚከበር ሆኖአል ። ቤተ ክርስቲያኒቱም አብራ እንደ መነኮሳቱ ተሠውራ እንድትታወቅ ልዑል እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ፰፻፰ ዓመት ሰው ሳያውቃት ከቆየች በኋላ እንደገና ከዘዚሁ ቡልጋ ሚባል ሀገር ፰፻፰ መናኞች የፊተኞቹ መናኞች አባቶቻቸው በደረሱበት መጋቢት 27 ቀን በዓጼ ወሰን ሰገድ መርሐነ ክርስቶስ ዘመነ መንግሥት አብረንታንት ገቡ ወዲያው የተሠወሩት አባቶቻቸው ተገልጸው ለነሱ ጌታችን እንዳደረገላቸው በዮርዳኖስ ውሃ አጥምቀው የድንጋይ ቆብ ቀርጸው አደረጉላቸው ማለት አመነ ኩሉአቸው በግብረ አምላክ በተሠራችውም ቤተ ክርስቲያን ቀድሰው አቆረቧቸው ።

የነሱን ትሩፋት የሚናገረውን በግብረ አምላክ የተጻፈውን ታሪክ ሰጥተው ተሠወሩአቸው ቤተ ክርስቲያኗ ግን ሳትሠወር ተተኪዎቹ አበው መነኮሳት እንዲጠቀሙባት ብዙ ጊዜ እንደቆየች በወለተ ጴጥሮስ ምክንያት ተሠውራለች። ይባላል ።

እነዚህ አበው አባቶች ከአባቶቻቸው እጅ የተቀበሉት መጽሐፍ እንደሚያዘው ጸንተው ቋርፍ እየተመገቡ ከል እየለበሱ ሥርዓተ ምንኩስናን እያስተማሩ ለተተኪዎች አበው መነኮሳት እንዲተላለፍ አደረጉ ። ከዚህ በኋላ



፵፰ መናኞች መጡእነሱም ከፊተኞቹ አበው ልጅነት ተቀብለው ሥርዓተ ገዳሙን በማጽናትና በመጠበቅ ገዳሙ እየሰፋ መናኙ እየበዛ ይሄድ ጀመር ከዚህ በኋላ በዓጼ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት የአክሱሙ ተወላጅ ስመ ጥሩው ጻድቅ አባ ሳሙኤል በፈቃደ እግዚአብሔር ከደብረ ዓባይ መጥተው በአበው መነኮሳት ተመርጠው አበ ምኔት ሁነው ብዙ ትሩፋት የሚሠራበት ታላቅ ስመ ጥሩ ገዳም አደረጉት ከዚህ በፊት አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በቆረቆሩት ደብረ በንኮል ሙራደ ቃል ገዳም ብዙ ትሩፋት ከሠሩ በኋላ ከአናብስትና ከአናምርት በስተቀር የሰው ድምጽ ወደ ማይሰማበት ጫካ ዛሬ ደብረ ዐባይ ወደ ተባለው ገዳም ገብተው ቦታውን አቅንተው ካሰፉትና ገዳም ካደረጉት በኋላ ከዋልድባ ገዳም አንድነት ገባ ገዳማውያኑን አበው በማስፈቀድ አንድ ማኅበር አደረጉት በዋልድባ ቋርፍ የማይበላ ተሐራሚ መነኩሴ ወደ ደብረ ዐባይ ተሻግሮ ጥራጥሬና ዳቤ ወይንም ንፍሮ እንዲቀምስ ፬ኛ ማይ ለበጣ ላይም እንዲቀመስ ሆኖአል ። በደብረ ዓባይ ገዳም የሚገኘው መሬት ጥራጥሬና እህል እንዲለማበት ለዋልድባ ገዳም ርስትም ሆነ ገንዘብ ወይንም ልብስ የሚሰጥ በጎ አድራጊት በደብረ ዐባይ በኩል በዋልድባ መነኮሳት ወኪል እንዲሰጥ ስጦታ ሁሉ በደብረ ዐባይ እንዲሆን ከዋልድባ መነኮሳት ጋር በስምምነት ከወሰኑ ባኋላ ብዙ ትሩፋት በዋልድባ ገዳም ሥር በዚሁ በደከሙበት ገዳም በዋልድባ አርፈው ተቀብረውበታል ።

በዚህም ትሩፋታቸው ፀሐይ ሳሙኤል ዘዋሊ ፀሐይ ሳሙኤል ዘዋልድባ ተብለዋል ።

ከዚህ በኋላ ከአባ ሳሙኤል ቀጥለው በቅድስና የታወቁት አባ በኪሞስ የሚባሉ ታላቅ ጻድቅ መነኩሴ ተሾሙ እርሳቸውም የታላቁን ጻድቅ የአቡነ ሳሙኤልን ሥርዓትና ወግ ከጥንት በሥርዓተ አበው የተወሰነውን ሕግ ጠብቀው ብዙ ቀን ሲያስተዳድሩ ከቆዩ በኋላ በዚሁ በዋልድባ አርፈዋል ።

ከዚህ በኋላ አባ ገብረ ክርስቶስ አባ ገብረ መስቀል አባ አናንያ አባ እስጢፋኖስ አባ ሙሴ አባ ሰላማ ገብርኤል የሚባሉ ከሸዋ ክፍለ ሀገር ቡልጋ ውስጥ ተነሥተው ከዚህ ከዋልድባ መጥተው ስለተቀመጡ በአባ ገብረ ክርስቶስ መምርነት የገዳሙ ሥርዓት እያማረ ገዳሙ እየሰፋ መናኞቹ እየበዙ ይሄዱ ጀመር



አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ

አባ ገ ክርስቶስ የኪዳን ምሕረትን ታቦት ተክለው እነዚህም መነኮሳት ፍጹማንና ተሐራምያን ስለነበሩ ልዩ ልዩ ተአምራት ይሠሩ ነበር የገዳሙ መነኮሳት ከመብዛታቸው የተነሣ በ፵ ደወል ተከፋፈሉ ዝቅ እያሉ ሲሄዱ ደግሞ ወደ ፴፱ ደወል ሁነዋል። በመጨረሻም ከዚያም አባ ሚናስና ጣዕመ ክርስቶስ የሚባሉ ታላላቅ መነኮሳት ሲመጡ ከ፴፱ ወደ ሁለት ደወል ዝቅ ብለዋል በነዚህም መነኮሳት ስም የሚናስና የጣዕመ ክርስቶስ ደወል ተብሎ በሁለት ደወል ተወስነው ይገኛሉ። ዛሬ በዋልድባ የሚገኙት መነኮሳት ብዛት በአንድ ሺህ ይገመታል ።

በዚህም ታላቅ ገዳም የቁም ጽሕፈትና የሥዕል የድጉሶች የጥራዝ ባለሙያዎች ስለሚገኙበት በሺህ የሚቆጠሩ በብራና የተጻፉ ዳዊቶችና አርጋኖን ውዳሴ አምላክ ወንጌለ ዮሐንስ ሌላም ብዙ የጸሎት መጻሕፍቶችና የሃይማኖት የታሪክ መጻሕፍቶች እንደክምር ተከምረው ይገኛሉ ።

ሥዕልም እንደዚሁ በየመነኮሳቱ ቤትና በቤተ ክርስቲያኑ ያማረ የደመቀ ሥዕል ይገኛል ። በገዳሙ ውስጥ የሚገኙት ቤተ ክርስቲያኖች የሚከበሩት የመጋቢት መድኃኔ ዓለምና የየካቲት ኪዳነ ምሕረት የነሐሴ ኪዳነ ምሕረት ነው ከሰዓታትና ከቅዳሴ በስተቀር ከበሮ በፍጹም አይመታበትም የኀዘን እንጅ የደስታ ነገር አይደረግበትም በዚህ ሁናቴ ገዳሙ ከጥንት ጀምሮ እስከአሁን ለወደፊቱም ገዳሙ በመንፈሳዊ ዓለም ተወስኖ የሚኖር ፍጹም ገዳም ነው ።

በዋልድባ ገዳም በኢትዮጵያ አውራጃዎች ሁሉ ይገኙ የነበሩት አበው ቅዱሳን ከገዳሙ በረከት ለማግኘትና ሱባኤ ለመግባት እየመጡ የጸለዩበት ቅዱሳን ብዙዎች ናቸው ከብዙዎቹ የታወቁት አቡነ አረጋዊ ቅዱስ ያሬድ አቡነ አባ በጸሎተ ሚካኤል አባ ኢየሱስ ሞዓ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘደብረ ሊባኖስ የመሳሰሉት ቅዱሳን ሁሉ ለሱባዔ ሁለት ሱባዔ ከዚያም በላይ ሱባዔ በማድረግ ተጠቅመውበታል የቀደሙ ነገሥታትም እየሄዱ ብዙ ተማህጽኖ እያደረጉ ተመልሰውበታል ብዙ የነገሥታት ልጆችም መንፈሳዊ ትምህርት ተምረው ተመልሰውበታል የውጭ አገር ሰዎችም ይህንን ገልጸዋል ። የዋልድባ ታሪክ

በጣም ሰፋ ያለ ስለሆነ ባጭሩ ታሪኩ ይህን ይመስላል ።

አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

ሊቀ ሊቃውንት ሞገስ ዘወልደ ማር ያም በጎንደር ክፍለ ሀገር ሊቦ አውራጃ በለሳ ወረዳ ስለ ወይና አቦ ከእናታቸው ከወይዘሮ ኅብረት እሸት ከአባታቸው መምህር ዘወልደ ማርያም በ፲፰፻፹፭ ዓ.ም ተወለዱ ፡ ዕድሜያቸው ለትምህ ርት ሲደርስ ወላጅ አባታቸው መምህር ዘወልደ የተማሩ ሊቅ ስለነበሩ የተወለ ዱበትን የወላጆቻቸውን ቤት ሳይለቁ ከወላጅ አባታቸው ከፊደል ጀምረው እስከ ዳዊት ተምረዋል ፡ በቃል ትምህ ርትም በኩል ውዳሴ ማርያምና መስተ ጋብዕ ፡ አርባዕት አርያም ሰለስት ወዘተ ተምረዋል ።

ከዚያ በኋላ ደብረ ትቦር ከነበሩት አ ለቃ ወልደ ሥላሴ ጽዋትወ ዜማን በሚ ገባ አጠናቅቀው ተምረዋል ወደጐንደ ርም ከተማ በመሄድ የአቋቋም ትምህር ታቸውን በሚገባ ተምረው ለማስተ ማር ከበቁ በኋላ ወደጐጃም ሀ ስብከት ሂደዋል ከዚያም ዋሸራ ማርያም ከምት ባለው ደብር ከነበሩት መምህር ደለለኝ ከተባሉት ሊቅ ቅኔ ከእነአገባቡ በሚገ ባ ተምረዋል ።

በዋሸራ ማርያም የቅኔ ትምህርታቸ ውን ካጠናቀቁ በኋላ የሊቃውንት ቦታ በመሆን ዝናው ወደታወቀው ሞጣ ቅ ዱስ ጊዮርጊስ ሂደው በሊቅነታቸው ከ ታወቁት መልአከ ገነት ጌታሁን የሐዲ ሳትን ፡ የፍትሐ ነገሥትን ፡ የሃይማኖተ አበውን ፡ የዳዊትን ትርጓሜ በሚገባ ተ ምረው ለማስተማር ከሚያስችል የዕው ቀት ደረጃ ደርሰዋል ።

ከሞጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ወደ ደብረ ታቦር ተመልሰው ከአለቃ ተስፋ የአፈ ወርቅን ትርጓሜ ሲያጠኑ ከአለቃ ብሬ ም የተክሌን አቋቋም ተምረው በመም ህርነት ተመርቀዋል ሊቀ ሊቃውንት ሞገስ ዘወልደ ማርያም በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጡ ጌታችን መድኃ ኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡን በም ሳሌ ሲያስትቦር "የመንግሥተ ሰማያ ት ደቀ መዝሙር የሆነ ጸሐፊ ሁሉ ከመ ዝገቡ አዲሱንና አሮጌውን የሚያወጣ ባለቤትን ይመስላል" ብሎ እንደተናገ ረው ሊቀ ሊቃውንት ሞገስ ዘወልደ ማ ርያምም ወደ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ ዝምብለው አልተቀመጡም ።

መናገሻ ፡ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ መኖሪያቸውን አድርገው የተክሌ አቋቋምን እያስተማ ሩ ፡ መጻሕፍተ ሊቃውንትን ፡ ሃይማኖ ተ አበውን ፡ ቄርሎስን ፡ መጻሕፍተ መ ነኮሳትን ፡ የቁጥር መጻሕፍትንና በጠቅ ላላው የመጻሕፍተ ሊቃውንት ትርጓሜ ን ከታወቁት የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ዶ ክተር አየለ ዓለሙ ፡ ለማጣራትና ምሥ ጢራቸውንም ለማስፋፋት ችለዋል ።

በ፲፱፻፴፩ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ከታወቀችው የዳግማዊ ምኒልክ መታ ሰቢያ ታዕካ ነገሥት በዓታ ገዳም የመ ምህራንና የቀሳውስት ማሠልጠኛ ገብ ተው ሊቀ ማዕምራን እየተባሉ በመጠ ራት የመጻሕፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ ላልተማሩት በማስተማር ብዙ ደቀ መዛ ሙርትን አስተምረው ለመምህርነት በ ማብቃት ለቤተ ክርስቲያናችን አበርክ ተዋል ።

ሊቀ ሊቃውንት ሞገስ ዘወልደ ማር ያም በቅኔም ትምህርት ከፍ ያለ ዕውቀ ት ነበራቸው ሊቁ ለቤተ ክርስቲያናችን ያበረከቱት መንፈሳዊ አገልግሎት በብ ዙ አቅጣጫ በመሆኑ በዚህ ጠባብ ዓም ድ ላይ ተንትኖ አንድ በአንድ ለአንባ ብያን ለማቅረብ ስለማይቻል በኃጭሩ ገትተነዋል ።

ሊቀ ሊቃውንት ሞገስ ዘወልደ ማር ያም ይህ ሁሉ አገልግሎታቸውና ችሎ ታቸው ታውቆና ተመዝኖ በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ የምትገኘው የታ ዕካ ነገሥት በዓታ ማርያም አስተዳዳሪ በመሆን ሊቀ ሊቃውንት ተብለው ተሹ መዋል ።

ሊቀ ሊቃውንት ሞገስ ቃለ እግዚአ ብሔር ወዳጅ በመሆናቸው ጉባኤ ሳያ ሁዱ የዕለት ትግባራቸውን አይጀምሩ ም ነበር እኒህ ሊቅ አንድ ቀን ጉባኤያቸ ውን ሳያጥፉ በተወለዱ በ፺፩ ዓመታቸ ው ጉባኤ ዘርግተው ማስተማር በጀመ ሩ በ፺፩ ዓመታቸው ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፸፮ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። በአዲስ አበባ የሚኖሩ ካህናትም በጸሎ ተ ፍትሐቱ ላይ በመገኘት ለሊቃውን ቱ የሚገባውን አደራረስ ፈጽመውላቸ ዋል በፍትሐቱ ላይ ከደረሱት ቅኔዎች ሁለቱን ቀጥለን አቅርበናቸዋል ።

፩ኛ/ ሥላሴ ቅኔ

ከአለቃ ይኄይስ መኰንን

ክልኤሆሙ ፍቁራን ፡ ሃይማኖተ አበው ወቄርሎስ ምስለ አፈ ወርቅ ዮሐንስ ዘበምሥጢሮሙ ኃብሩ ፡ እምዮም እስከ ለዓለም ሕቡረ ተቀብሩ



ሊቃ ሊቃውንት ሞገስ ዘወልደ ማርያም

እስመ ረከቡ ሞገስ ዘወልደ ማርያም ዶ ዝክሩ ፡
ስመ ወልደ ሥሉስ ለዘአመሩ ፡
እምነ ሕማም ወሞት በበብሔሩ
እስከ ርእሱ እምዘ ቆመ እግሩ

፪ኛ/ሥላሴ ቅኔ

ከግራ ጌታ ሀብቴ ወልደ ዮሐንስ

ኢትጽላዕ ሞተ ሥጋ ፡ ምስለ ሊቅ ገቢረ ወተሰዕሎ ፡ በዘቦ ዕድሜከ ዕድ ሜ ማቱሳላ ርሑቅ ምስለ ሊቅ አኮኑ ዘ ወአለ ሊቅ
ወእመ ጥበብከ ዓብየ እምኩሉ ኬነውተ ዓለም ዕውቅ
ከይንኮ ሐዲሰ ሞገስ ጽድቅ
ለቤትከ ዝጎር እንተ የሐልቅ
በብሩር ካልኡ ለወርቅ

ወደ አማርኛ ሲተረጐም

የሥጋ ሞት ሆይ ዕድሜህ እንደማቱ ሳላ የረዘመ ሽማግሌ ብትሆንም ከሊቅ ጋር ጥያቄ ማድረግን አትተው ከሊቅ ጋር የሚውል ሊቅ ነውና ፦

ጥበብህም ከዓለም ጥበበኞች የታወ ቀ ስለሆነ ቤትህን መቃብር በሊቀ ሊቃ ውንት ሞገስ ሥጋ ፡ ለወርቅ ሁለተኛ በ ሆነ ብር ከደንከው ማለት ነው ፤

በቀብሩም ሥነ ሥርዓት ላይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢት ዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲ ያን ፓትርያርክ ፡ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የጉባኤ መምህራን ፡ ካህናትና በሺህ የ ሚ ቆጠሩ ምእመናን ተገኝተዋል ።

ሊቀ ሊቃውንት ሞገስ ዘወልደ ማር ያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "በጸጋ ዘንሣዕክሙ በጸጋ ሀቡ" ዋጋ ሳትሰጡ የተማራችሁትን ዋጋ ሳትቀበሉ አስተ ምሩ ያለውን አምላካዊ ቃል በመከተል ብዙ ደቀ መዛሙርትን አስተምረው ለ ቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ። ሊቁ ቅዱሳት መጻሕፍትን መመልከት ቤተ ክርስቲያንን ማገልገልና ማስተማ ር የዘወትር ተግባራቸው ነበር ።

እንደነዚህ ያሉት ሊቅ በሞት ሲለዩ ቤተ ክርስቲያናችን የምትጽናናው አስ ተምረው ባበረከቷቸው ደቀ መዛሙር ት ነው ስለዚህ ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ቅን አገልግሎታቸው ታሪካቸውን መዝ ግባ ለተከታይ ትውልድ ታስተላልፋ ለች ።

ከተዕካ ነገሥት በዓታ

# አንጢላርዮስ

አንጢላርዮስ የተባለው ባለጸጋ ለተ ቸገረ ድኃ የማያዝንና የማይሠጥ ንፉግ ነበረ ከዕለታት አንድ ቀን ነዳያን በመ ንገድ ተቀምጠው ሣለ አንጢላርዮስ ሲያልፍ አይተው ይህ ጽኑ ጨካኝ ባለ ጸጋ ለተቸገረ ሰው አያዝንም ተባባሉ ። ከመካከላቸው አንዱ ግን ሄጄ ሠጥቶኝ በልቼ ጠጥቼ ብመጣስ? ፡ አብልቶህ አጠጥቶህ አትመጣም እንዲያውም አይሠጥህም ሲሉ ተወራርደው ሄደ። ባለጸጋውም ምግብ አቅርቦ ሊመገብ ሲል ችግረኛው ድንገት ደረሰና የእግዚ አብሔርን ስም ጠርቶ ከሚመገበው ምግብ እንዲሠጠው ለመነው አንጢ ላርዮስም አንስቶ እንዳይሠጠው ራሱን ርቦታል ፡ እንዳይከለክለውም ችግረኛው የእግዚአ ሔርን ስም ጠርቶ ለምኖታል ፡ በዚህ ተናደደና ዳቦውን ወርውሮ የችግ ረኛውን ሰው ግንባር ገመሰው (ፈነከ ተው) ለማኙም ድኃ ደሙን ጠርጐ ከዳ ቦው ጕረሰለትና ጥቂት ለምልክት ይዞ ወደተወራረዳቸው ጓደኞቹ ዘንድ ሄደ ።

በዚሁ ሌሊት አንጢላርዮስ ራእይ ያያል ። ራእዩም እንዲህ ነበር ፦ "ነፍ ሱ ከሥጋው ተለይታ መላእክተ ጽል መት እያዳፉ ይዘውት ሲሄዱና መላእክ ተ ብርሃንም ከኋላ ሲከተሏት ፡ መላእ ክተ ብርሃንን መላእክተ ጽልመት እና ንተ ከዚች ነፍስ ምን አላችሁና ትከተሏ ታላችሁ በማለት ሲጠይቋቸው ያያል መላእክተ ብርሃንም ምነው ትናንት ለተ ራበ ድኃ አብልቶ የለምን ብለው ሲመ ልሱላቸው ፤ መታው እንጂ ለድኃው መቸ ሰጠው በማለት ይከራከሯቸዋል በዚህ ጊዜ ራሱ ደኃው ይመሰክር ይመስ ክር ተባብለው ወደ ደኃው ሄዱና መስ ክር አሉት ። ድኃውም ትናንት ያጠገብ ከኝ ባለጸጋ ሆይ ከዚህ አመጡህን?ከረ ሃቤ ጽናት የተነሣ በትሩ አልታወቀ ኝም ብሎ ሲመሰክርና መላእክተ ብር ሃን ከመላእክተ ጽልመት ነፍሱን ሲቀ በሏት አየ ።

ሲነጋ በዚህ ዓለም ገንዘብ ሳያውቁ የሰጡት እንዲህ ያስጠቀመ አውቀውና ወደው የሰጡት ምን ያህል ያስጠቅም ብሎ ነዳያንን (ችግረኞችን ሰብስቦ ያለ ገንዘቡንና ንብረቱን ሁሉ ጨርሶ ሠጥ ቶ (አከፋፍሎ መንኖ ሲሄድ ነዳያን ከመ ንገድ አገኙትና ገንዘብ ትሠጣለህ ቢሉ ን ወዳንተ መጥተን ነበር አሉት ንብረ ቱንና ገንዘቤን ሣልጨርስ መጥታችሁ ቢሆን ከፍየ እሰጣችሁ ነበር ። አሁንማ ጨርሻለሁ አላቸው መልሰው እኛን ርቦናል ጠምቶናል እንዴት እንሁን አሉት እርሱም እኔን ሸጣችሁ ተካፈሉ አላቸው ። ለነዳያንስ አልቦሙ ምህረት ይላልና ።

ለሠላሣ ወቄት ሸጠው ገንዘቡን ተካ ፍለውታል ። እርሱም በተሸጠበት አገር ሲያርስ ውሎ ማታ ከደረቅ ቦታ ሣር አለምልሞ ከደንጋይ ውሃ አፍልቆ ሲያር ስባቸው የዋላቸውንና የሚጠብቃቸውን ከብቶች ይመግባል ። ይህንን ኃይለ እግ ዚአብሔር የመላበት ታምራታዊ ሥራ የተመለከቱ ሁሉ ዕፁብ ዕፁብ ሲሉ ከተወለደ ጀምሮ ተናግሮ የማያውቅ ዲዳና ሰምቶ የማያውቅ ደንቆሮ ነበሩ በትንፋሹ አፍ ቢላቸው ዲዳው ተናግ ሯል ፤ ደንቆሮው ደግሞ ሰምቷል ። በዚ ህም ክብር ስለሰጡት ተገለጸብኝ ብሎ ተሠውሯል ።

ከዚህ በላይ ከባለጸጋው ታሪክ እንደ ተረዳነው ሁሉ በዚህች ሐላፊና ጠፊ ዓለም ለተወሰነ ጊዜ የምንቆይ እንጂ እስከ መጨረሻው ድረስ ዘላቂ ወይም ቀዋሚ አለመሆናችንን ነው።ሆኖም ማ ንም ሰው በሥጋው ቢሞት መልካምና ቋ ሚ ሥራ ሠርቶ ካለፈ በሥጋው ይሙት እንጂ ስሙና ነፍሱ ሕያዋን ሁነው ይኖ ራሉ የተሠጠውም የገንዘብ ጸጋ ብልና ዝገት በማያጠፉት ቦታ ሌባም ቆፍሮ በማይሠርቀው ዘለዓለማዊ መዝገብ ተቀመጠ እንጂ አለቀ ማለት በጣም መሣሣት ሆኖ እናገኘዋለን ።

ወደ ገጽ ፲፬ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# "ጠባቆችን እሰጣችኋለሁ"

ትንቢተ ኤርምያስ ፫. ፲፭ መንጋዎች ከሌሉ እረኞች አይኖሩም ረኞችም ከሌሉ መንጋዎች የመኖር ዋስትና ሊኖራቸው አይችልም ከመንጋዎች ይልቅ ከጠባቆች የሚፈለገው አገልግሎት እጅግ በጣም የላቀ ይሆናል ።

መንጋዎች የለመለመ ሣር ነጭተው ቅጠል በጥሰው ውሀ ተጐንጭተው እንዲጠግቡ እንዲራቡና እንዲሰቡ እረኞች በንቃትና በትጋት ይጠብቋቸዋል አውሬ እንዳይበላቸው ሌባ እንዳይሠርቃቸው ወድቀው እንዳይሰበሩ ገደል ገብተው ሕይወታቸውን እንዳያጡ ብርቱ ጥንቃቄ ያደርጉላቸዋል ፤ ከአቅማቸው በላይ የሆነ ተጻራሪ ነገር ቢገጥማቸው እንኳን ሕይወታቸውን አሳልፈው ከመስጠት ወደኋላ አያፈገፍጉም ።

ይህንን የሚያደርጉት እውነተኞች ጠባቆች ሲሆኑ በእነርሱ አንጻር ደግሞ ስለመንጐቻቸው የማያስቡ ሰነፎች እረኞች መኖራቸውን መዘንጋት የለብንም ሰነፎች እረኞች ስለመንጋዎቻቸው ትክክለኛ የሆነ አስተሳሰብ የላቸውም መንጋዎቹን አውሬ ቢበላቸው ሌባ ቢሠርቃቸው ጉድጓድ ገብተው በገደል ተንከባለው ሕይወታቸውን ቢያጡ ደንታ አይኖራቸውም ፤ በምግብም በኩል ወደለመለመ ሣርና ቅጠል ወደጠራ ውሀ አያሠማሯቸውም ፤ ከመንጋዎቹ የሚገኘውን ጥቅም ይፈልጋሉ እንጂ ለመንጋዎቹ የሚያስፈልጋቸውን አያዘጋጁላቸውም ።

በቅዱሳት መጻሕፍት እረኞች በመምህራንና በመሪዎች መንጋዎች በምእመናን እየተመሰሉ ተጽፈዋል እግዚአብሔር አምላክ በዘመኑ እሩት ለአስተማሪነትና ለመሪነት ሥልጣን እንዲኖራቸው አድርጐ ብዙዎቹን የመረጣቸው ከበግና ከላም እረኝነት መሆኑ የታወቀ ነው ።

እንደዚህ ካለ ዝቅተኛ ሥራ ሳሉ ለከፍተኛ ተግባር የተመረጡትም መሪዎችና አስተማሪዎች ለሚመሩአቸውና ለሚያስተምሯቸው ሕዝቦች ሕይወተ ሥጋቸውን አሳልፈው ለሞት ለመስጠት የተዘጋጁ እንደነበሩ ከቅዱሳት መጻሕፍት እንረዳለን ።

ለማስረጃ ያህል ጥቂቶችን ቀጥለን እንመልከታቸው ነቢዩ ሙሴ የአማቱን የዮቶር የምድያም ካህን በጎችን ይጠብቅ ነበር ከዕለታት አንድ ቀን በጎቹን በኮሬብ ተራራ እሠማርቶ ሲያበላ እግዚአብሔር በእሳት ነበልባል ተገልጦ እኔ የአባቶችህ የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ነኝ ብሎ አምላክነቱን ከገለጸለት በኋላ ወደፈርዖን እልክሃለሁ ሕዝቤን እስራኤልን ከግብፅ ምድር ታወጣለህ በማለት ለብዙ ዘመናት በባርነት ቀንበር ሥር ወድቀው የነበሩትን እስራኤል ከባርነት ነፃ እንዲያወጣ



እውነተኛ ጠባቂ ለበጎቹ ያዝናል

ቸው አድርጐታል ሕዝቡም በሙሴ መሪነት በእግዚአብሔር ቸርነት ከግብፃውያን የባርነት ቀንበር ከተላቀቁ በኋላ ሙሴ ሕዝቡን የሚያስተዳድርበት ሕግ ከእግዚአብሔር ለመቀበል ወደ ሲና ተራራ ቢወጣ ሕዝቡ የጥጃ ምስል አቁመው በመስገድ አምላካቸውን እግዚአብሔርን በደሉ ።



እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ተቆጥቶ ሕዝቡ በድለውኛልና አጠፋቸዋለሁ አንተን ግን ከዚህ በበለጠ ሕዝብ ላይ እሾምሀለሁ ሲል ለሙሴ ነገረው ነቢዩ ሙሴም እውነተኛ ጠባቂ በመሆኑና ስለሕዝቡ የሚያዝንና የሚራራ ስለሆነ ሕዝቡን ከምታጠፋቸው ይልቅ እኔን ከባለሟልነትህ ፋቀኝ በማለት ሕይወቱን ስለሚጠብቃቸው ሕዝቦች አሳልፎ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን ገልጾ ወደ ፈጣሪው ለመነ እግዚአብሔር አምላክም የሙሴን ልመና ሰምቶ ሕዝቡን ይቅር ብሏቸዋል "ዘፀ.፫. ፭ ፡ ፴፪.፴"

ነቢዩ ዳዊትም ሕዝቡን እንዲመራ የተመረጠው የአባቱን የዕሤይን በጐች እየጠበቀ ሳለ ነበር ፤ ስለ አመራረጡም ራሱ ሲገልጽ እኔ ከወንድሞቼ ይልቅ ታናሽ ነበርኩኝ በአባቴ በዕሤይ ቤትም ደቦል ሕፃን ነበርኩኝ የአባቴን በጐች እጠብቅ ነበር እጆቼም መሠንቆ ይመቱ ነበር ፤ ጣቶቼም በገናውን እያስማሙ ይደረድሩ ነበር ለጌታዬ የእኔን ነገር ማን ነገረው እርሱ እግዚአብሔር አዋቂ ነው ሰማኝ መልአኩንም ልኮ አዳነኝ የአባቴን በጎች ከምጠብቅበትም መርጦ ወደደኝ ወንድሞቼ አዋቆች ያማሩና የተወደዱ ነበሩ ነገር ግን እግዚአብሔር በነርሱ አድሮ ለመመስገን አልወደደም" ብሏል መዝ ፻፶፩

በእግዚአብሔር ፈቃድ ከበግ ጠባቂነት ለሕዝብ ጠባቂነት የተመረጠው ነቢዩ ዳዊት በደስታም ሆነ በመከራ ከሕዝቡ ጎን አልተለየም ነበር አንድ ጊዜ ፈጣሪውን እግዚአብሔርን አስቀየመና ነቢዩ ጋድ ወደ እርሱ ሂዶ ስለሠራው በደል ሦስት መከራዎች የታዘዙበት መሆናቸውን ገልጾ ከሦስቱ አንደኛውን ምረጥ አለው ።

የታዘዙትም መቅሠፍቶች እነዚህ ነበሩ ፡-

፩ የሦስት ዓመታት ረሀብ በሀገርህ ይምጣብህን

፪ ወይስ ጠላቶችህ እያሳደዱ ሶስት ወራት ከእነርሱ ትሸሽን

፫ ወይስ ሦስት ቀኖች ቸነፈር በሀገርህ ላይ ይሁን አለው ነቢዩ ጋድ ይህንን ለዳዊት በነገረው ጊዜ ደነገጠና እጅግ በጣም ተጨንቄያለሁ በሰው እጅ ከመውደቅ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ ይሻለኛል ምሕረቱ ብዙ ነውና በማለት ቸነፈሩን መረጠ ወዲያው ሰባ ሺህ ሕዝብ አለቀ ነቢዩ ዳዊት የሚቀሥፈውን መልአክ ባየ ጊዜ ስለ ሕዝቡ በጣም አዘነና እኔ እግዚአብሔርን በድያለሁ ፡ ክፉ ሥራም ሠርቻለሁ እነዚህ በጎች ምን አደረጉ እጅህ በእኔና በአባቴ ቤት ላይ እንድትሆን እለምንሃለሁ በማለት ወደ ፈጣሪው በመጸለይ መቅሠፍቱ እንዲያቆም አድርጓል ። ፪ኛ ሳሙ ፳፬. ፲፪ - ፲፯ ።

ከደቂቀ ነቢያት አንዱ አሞጽ ከላም ጠባቂነት ተመርጦ ሕዝበ እስራኤልን በመምከርና በማስተማር ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ እንዲመለሱ አድርጓል ይኸው ነቢይ ስለመመረጡና ይሠራው ስለነበረው ተግባር ሲናገር "እኔ ላም ጠባቂና ወርካ ለቃሚ ነኝ እንጂ ነቢይ የነቢይ ልጅም አይደለሁም እግዚአብሔርም በጎቼን ከመጠበቅ ወሰደኝ ሒድ ለሕዝቤም ለእስራኤል ትንቢት ተናገር አለኝ ብሏል አሞጽ ፯. ፲፬

እንዲሁም ነቢዩ ዘካርያስ እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ የሰነፍን እረኛ ዕቃ ውሰድ እነሆ በሀገሩ ውስጥ እረኛ አይፈልግም የተሠበረውንም አይጠግንም የከሳውንም አይቀልብም ነገር ግን የሰባውን ሥጋ ይበላል ሰኰናውንም ይቀለጣጥማል ይልና መንጋውን ለሚተው ለሰነፍ እረኛ ወዮለት ሰይፍ በክንዱና በቀኝ ዓይኑ ላይ ይሆናል ክንዱም እጥብቃ ትደርቃለች ቀኝ ዓይኑም ፈጽማ ትጨልማለች በማለት ተናግሯል ዘካ. ፲፩. ፲፯

ለማስረጃ ያህል ጥቂቶቹን ጠቅሰን ተናገርን እንጂ ስለሕዝቦቻቸው ራሳቸውን ለሞት አሣልፈው የሰጡ መሪዎችና አስተማሪዎቅ ቁጥራቸው ብዙ ነው ።

ጠባቂዎችን እሰጣችኋለሁ ብሎ ነቢዩ ኤርምያስ እንደተናገረው ቅድስት ቤተ ክርሳቲያናችን ለወገኖቻቸው እንደራሳቸው አድርገው የሚያስቡና የሚጠነቀቁ መንፈሳውያን ጠባቂዎችን እያገኘች ናት ።

በተለይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስስቲያን ፓትርያርክ ሆነው ከተሠየሙ ወዲህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን በንቃትና በትጋት የሚያስተምሩና የሚመሩ ብፁዓን አባቶች ስላገኘች የነቢዩ ቃለ ትንቢት ትርጉሙን አግኝቷል ለማለት ያስደፍራል አገልግሎት የሚፈለገው ከጠባቂዎች ብቻ ሳይሆን ከተጠባቂዎቹም ጭምር ነውና የእግዚአብሔርን ቃል ከመምራን የተማሩ ምእመናን ሁሉ ተገቢውን አገልግሎት ለእግዚአብሔር የማቅረብ መንፈሳዊ ግዴታ አለባቸው ።



የባጎች ጠባቂ

ሐዋርያው ጳውሎስ "ብዙ ጊዜ በእርሷ ላይ የሚወርደውን ዝናም የምትጠጣ መሬት ለሚያርሱአት ገበሬዎች ደግሞ የሚጠቅሙ አዝርዕቶችንና አትክልቶችን ታበቅላለች በረከትን ግን ከእግዚአብሔር ታገኛለች ይህንን ትታ እሾህንና አሜከላ ብታበቅል የተጣለች ትሆናለች ለመርገምም ትቀርባለች መጨረሻዋም በእሳት መቃጠል ነው" በማለት እንደተናገረው ፤ ምእመናን ከመምህራን የሚነገራቸውን ትምህርት አዳምጠው እግዚአብሔርን በማመን ጸንተው መልካም ሥራ መሥራት አለባቸው ።

የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው በጎ ሥራ ካልሠሩ ግን የ መጨረሻው ዋጋቸው ፍዳ ይሆናል በነቢዩ በኤርምያስ አድሮ ጠበቆችን እሰጣችኋለሁ ብሎ የተናገረአምላክ አሁን ጠባቂዎች ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን እንዲሁም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ሰጥቶናል ።

ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክና ከብፁዓን አባቶቻ የሚሰጠውን ትምህርት አዳምጠ በመልካም ሥራ ላይ ማዋሉ ግን የሰማእያኑ ምእመናን ፋንታ ነው ።

ቄ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ



www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## ቅድስት አርሴማ

በሦስተኛው ክፍለ ዘመን የተፈጸመ ታሪክ ነው ። ዲዮቅልጥያኖስ ነግሦ በነ በረበት ዘመን የክርስትና እምነት እንደ ፀሐይ ጮራ በዓለም ላይ ተፈንጥቆ ስለ ነበር ይህንኑ ለማጨለም በዚያን ጊዜ ይደክሙ ከነበሩት አላውያን መካከል በክርስቲያኖች ላይ ሰፋ ያለውን እርምጃ በመውሰድ በጨካኝነት ስሙ እንደሚጠራ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያብራራል ። በዚህም አኳኋን ህብረተሰቡን አጠቃሎ የያዘውን አስተዳደር ወደ ጀርባው ትቶ የጣዖታት መቅደሶች ይከፈቱ የእግዚአብሔር ስም የሚጠራባቸው ቤተ መቅደሶች ይዘጉ ሲል አወጀ ኃይሉንም በዚህ ብቻ ወስኖ ሳይቀር ወዲያው ቀጠለና በክርስቶስ የሚያምኑ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እየተያዙ እንዲታሰሩ ከብዙ ቀንም እሥራት በኋላ ሥቃዩ የማይመራቸው ቢሆን በልዩ ልዩ ቅጣት እየተቀጡ እንዲገደሉ ወደ እቶን እሳትም እየተወረወሩ እንዲጣሉ የሚል ሕግ አውጥቶ በሚያስተዳድራቸው ክፍለ ግዛቶች ሁሉ ትዕዛዝ አስተላልፎ እንደነበር ይኸው ታሪክ በተጨማሪ ይናገራል ።

እንዲህ ያለውም ግፍ ይፈፀምበት በነበረው ወራት ከላይ የተጠቀሰችው ቆራጢ ክርስቲያን ሃይማኖታቸውን ለማስከበር ቆርጠው ከተነሱት ከ70 ማህበረ ደናግል መካከል አንደኛይቱ ነበረች እርሷም በምግባርና በሃይማኖትም የተዋበች ስለነበረች ከጓደኞቿ ጋር ሁና ይህን መሣፍን ሕገወጥ ትዕዛዝ ተቀውማ እርስቷንም ሆነ ቤቷን ትታ ከቤተሰቦቿና ከወገኖቿ ተለይታ ከጓደኞቿ ጋር መነነች ተራራ ለተራራም ተንከራተተች ይህች በክርስቶስ ታማኝ የሆነች ሴት ከጓደኞቿ ጋር ሆና ይህን ሁሉ መከራ በደስታ ተቀበለች ሃይማኖትዋን በተግባር ለማስመስከር አቅሟም እስከፈቀደላት ድረስ ታገለች ወደፊት እንጂ ወደኋላ ሳትል በእምነቷ ጸናች ቤቷንም ሆነ እርስቷን በእግዚአብሔር ፍቅር ለወጠች ጥሪውንም አክብራ ወደ ማታውቀው አገር ሄደች ።

የእሥራኤል ደናግል ባህረ ኤርትራን ሲሻገሩ ነፃነት ለሰጣቸው ለእግዚአብሔር እንደዘመሩና እንዳወደሱ ሁሉ አርሴማም ከአፍ እስከ ገደፍ ሞልቶ የነበረውን የሞት ባሕር ለመሻገር በጀመረች ጊዜ ከጓደኞቿ ጋር እንዲረዳት እግዚአብሔርን አመነች ወደ እርሱም ጸለየች ከጥቂት ጊዜም በኋላ ፸ ከሚሆኑ ማህበረ ደናግል ጋር አገር አቋርጣ ሔዳ አርማንያ ከሚባለው አገር ትኖር ጀመር ከዚያም እርሷና ጓደኞቿ የጸሎት ቤት አቋቁመው ሕዝብን ማስተማር ጀመሩ በመካከላቸውም አጋታ የተባለችውን መርጠው እመምኔት ሾመው ሥራውን ለማካሄድ ቆርጠው ተነሡ ።

የእነዚህም ማህበረ ደናግል ሥራቸው ተቃንቶ ብዙ የክርስቶስ ተከታይ የሆኑ ምእመናንን ሰብስበው በማስተማር ላይ ሳሉ ንጉሡ ዲዮቅልጥያኖስ አርሴማ የተባለችውን ክርስቲያን አርማንያ በሚባለው አገር መኖሯንና ስለ ክርስትናም እምነት ማስተማሯን ሰማ በዚህ ጊዜ የአርማንያ ንጉሥ ለሆነው ድርጣድስ ለተባለው እንዲህ ሲል ከዚህ የሚከተለውን መልእክት ላከበት ። በእኔ ግዛት ውስጥ የተወለደች ስሟ አርሴማ የተባለች መልከ መልካም የሆነች ሴት ትእዛዜን እንድትፈጽም ብነግራት አልፈጽምም በማለት ሕገ ወጥ ከመሆኗም ሌላ 69 ሴቶች ከእኔ ዘንድ አስከድታ አንተ በምትገዛው ሀገር አለች ማለትን ሰምቻለሁና እጅ ከፍንጅ አስረህ ብትልክልኝ ወረታህን እከፍልሃለሁ የሚል ነበር ።

የአርማንያም ንጉሥ የተጻፈለትን መልእክት ካነበበ በኋላ አርሴማን አስጠራት በጣም መልከ መልካም ሁና ስለ አያት እንዲህ ያለችውን እኔ አገባታለሁ እንጅ ለእርሱ አልክም የሚል ሥጋዊ ሃሣብ አደረበት ። ከዚህም የተነሣ ለደብዳቤው መልስ ለመጻፍ አልፈቀደም ። ወዲያውም አጋታ የተባለችውን እመምኔት አስጠርቶ በላያችሁ ላይ አንዳች ነገር እንዳፈጸምባችሁ እጠብቃችኋለሁ ለስብከትም ሆነ ሥራ ለመሥራት ከአንዱ ወደ ሌላው ቦታ እንድትዘዋወሩ ትዕዛዝ አስተላልፍላችኋለሁ ። ነገር ግን እኔ ይህን ሣደርግላችሁ እናንተ ደግሞ በአንድ በኩል ልታስደስቱኝ ይገባችኋል ። ይኸውም አርሴማ የተባለችው ሴት ደስ ስለአለችኝ ለጋብቻ እፈልጋታለሁና አንችም ፍቀጅልኝ እርሷንም ጠይቂልኝ አላት እርሷም እስቲ ለማንኛውም ነገር ልመካከር አለችና ወደ በአቷ ተመለሰች ከዚያም አርሴማን ጠራችና እንዲህ አለቻት በሃይማኖት የማይመስለን በምግባርም የማይስተካከለን ይህ አረመኔ እጮኛ እንድትሆነኝ አማልጅኝ ሲል ጠየቀኝ እኔ በበኩሌ

የምመክርሽ መርዓዊሃ ለቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን ሙሽራዋ ነው ለተባለው ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

ወደገጽ ፲፮ ዞሯል



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ ሥነሥርዓቶችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፐ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቁ. 116616
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org